


# ትንሣኤ



ቁጥር ፲፰

ኅዳር ፲፱፻፸፱ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፤ሥርዓትና ዜና፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

ዋና አዘጋጅ ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ
ም/ አዘጋጅ መ/ ክኅረ. ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

## ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን ስምምነት አለው | ፪ |
| ዘመነ ሚጠት | ፬ |
| አርባዕቱ እንስሳ | ፭ |
| መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በፈታኙ ይሑዳል | ፯ |
| የእግዚአብሔር ታቦት | ፱ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፲ |
| ክርስቲያናዊ ሕይወት | ፲፪ |
| ኪብዑዓን አባቶች አቡነ ያዕቆብ ሊቀ ጳጳስ | ፲፬ |
| ስብከተ ወንጌል | ፲፭ |
| ✓ ዜና ሊታውንምት | ፲፯ |
| አንደበት እሳት ናት | ፲፱ |
| ሃያ አራት ሽማግሌዎች | ፳ |
| የትንቢትና ምሳሌዎች ትርጉም | ፳፪ |
| ዘግይቶ የደረሰን ዜና ((የአዋሳ ካህናት ማሠልጠኛ | ፳፬ |

# ደብዳቤዎች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ፤
አዲስ አበባ ፤

በቅድሚያ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከሰላምታየ ቀጥየ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርቤ ያለሁና ተገቢ የሆኑትን መልሶች እንደምትሰጡኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

1ኛ/ ሥርዓተ ተክሊል ለመፈጸም የሚመጡትን ሰዎች መታወቂያ ካርድ ካላመጣህ ገንዘብ ካልከፈልክ ሥርዓተ ተክሊል አይፈጸምልህም በመጣህበት ተመለስ እያሉ የሚያሰናብቱ ካህናት አሉ ይህ ተገቢ ነውን ?

2ኛ/ የገሃድ ጾም ስንት ነው? (ለ) በጾም ወራት የታረደ የእንስሳ ሥጋ በብሉት ሊበላ ይችላል ወይ ? ዓሣስ በጾም ይበላል ወይ ? ሐ) በመላእክት በጻድቃንና በሰማዕታት ወዘተ ስም ማህበር የሚጠጡ ጽዋ ብለው ለሚጠሩት የሽክላ ዕቃ መስገድን ልምድ አድርገው የያዙ አልፎ አልፎ ይገኛሉ ይህ ተገቢ ነውን ?

3ኛ/ የቀረበው ጥያቄ ሳይቀነስ ሳይጨመርበት ለምን አይታተምም ?

4ኛ/ በንስሐ የማይሠረይ ኃጢአት አለን ?

5ኛ/ ለእመቤታችን ድንግል ማርያምና ለታቦት መስገድ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ መሳለም ለስዕልም መስገድ አይገባም የሚሉ ስላሉ ማስረጃ የሚሆን ጥቅስ ጻፉልን እባካችሁ ።

6ኛ/ ከካህናትም ሆነ ከምእመናን ከተጋቡ በኋላ አርባ ቀን እስኪመላቸው ድረስ ካህናቱ ገብተው እንዳይቀድሱ ምእመናኑም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ የሚከለክሉ አሉ ይህ እንዴት ነው ?

7ኛ/ ሥርዓተ ተክሊልና ጋብቻ በሚፈጸምበት ጊዜ ልጃገረዶች ደረታቸውንና ጡታቸውን የሚያሳይ ልብስ ለብሰው ሙሽሮቹን በማጀብ ቤተ ክርስቲያን ይገባሉ ይህ ተገቢ ነውን ?

መዘምር ሣህለ ሚካኤል ወልደ ኢየሱስ

ከሌማመር መድኃኔ ዓለም
የሰ ት ቤት ጽ ቤት

መልስ ፤

መዘምር ሣህለ ሚካኤል ወልደ ኢየሱስና የተዋህዶ ነጸብራቅ የሰንበት ቤት መዘምራን ስላቀረባችሁልን ሰላምታ ዓፀፋውን በመመለስ ዘመኑ ዘመነ ሰላም እንዲሆንላችሁ እንመኝላችኋለን ።

1ኛ ጥያቄ መታወቂያና ይህን ያህል ገንዘብ ካላመጣህ በመጣህበት ተመለስ ማለት ተገቢ ነውን ? ስለምትለው፡ መታወቂያ መጠየቅ ኃጢአት ወይም በደል አይደለም የየትኛው ቤተ ክርስቲያን አባል መሆኑ የሚታወቀው በመታወቂያው ነውና ስለ ገንዘቡም ቢሆን ይብዛ ይነስ አልታወቀም ለይተህም አልገለጽከውም ቢሆንም ሌሎች ተክሊል ሲደረስላቸው የሚከፍሉትን ያህል ከጠየቁህ ከበደል ሊቆጠር አይችልም ሌሎቹ ከሚከፍሉት በለጥ አድርገው ከጠየቁህ ግን ያጠያይቃል ።

የሆነ ሁኖ ማወቅና መገንዘብ ያለብህ ምሥጢረ ተክሊል ሲደርስ ብዙ ድካም ከፍ ያለም አገልግሎት እንዳለ ነው ።

ይኸውም ጧፍ የሻማ የመሳሰሉት ሥርዓተ ተክሊል መገልገያዎች አሉ ታድያ ለእነዚያ መግዣ መጠነኛ ገንዘብ ካልተከፈለ በምን ይገዛሉ ? እርግጥ ያለ ዓቅምና ሌሎቹ ያልተጠየቁትን ከጠየቁህ ያነጋግራል ስለዚህ የገንዘቡን ልክ ብትጽፍልን የተመቸ ነበር ።

የ2ኛው ጥያቄ ገሃድ ሁለት ናቸው እነዚህም 1ኛው የልደት ዋዜማ 2ኛው ደግሞ የጥምቀት ዋዜማ ናቸው እንስሳትም ቢታመሙ በጾም ማረድና በግድፍት መብላት ፈጽሞ ተገቢ አይደለም ስለ ዓሣ መበላትና አለመበላት ግን መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት የሚለውን መጽሐፍ ብትመለከት ተንትኖ ያስረድሃልና እሱን ተመልከተህ መልሱን ታገኛለህ በመላእክት በጻድቃንና በሰማዕታት ስም ማኅበር የሚጠጡ ሰዎች ጽዋ ብለው ለሚጠሩት ዕቃ መስገድ ተገቢ እንዳይደለና የቤተ ክርስቲያናችን ባህል ስላይደለ እኛም እንዳይሰግዱ እናስተምራለን እንመክራለን ከዚህ በፊት የተጻፉ ጥያቄዎች ለምን አልወጡም ስለ ምትለው ግን ይኑሩ አይኑሩ ጥያቄዎቹም ምን ዓይነት እንደሆኑ ስላላወቅናቸው ደግመህ ብትጽፍልን የተሻለ ነው ።

3ኛ/ የሚቀርበውን ጽሑፍ አርመንና የተሻለውን ቃል አስገብተን እናስተካክለዋለን እንዲህም ማለት የረዘመውን

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን ስምምነት አለው ?

ፀሐይ ሲወጣ ጨለማ ይርቃል ሌሊት ሲያልፍ መዓልት ክረምት ሲወገድ በጋ ይተካል ። የሁሉም ባሕርይ የተለያየ በመሆኑ በአንድ ጊዜ አንድ ላይ ሊገኙ አይችሉም ። እንዲሁም የክርስቶስ መንፈስ ባለበት የሰይጣን መንፈስ አይኖርም ። በዚህ ዓለም የሚኖር ሰው ሁሉ በሰውነቱ ውስጥ ከባድ ትግል አለበት ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ዓለመ ሥጋ በነበረበት ጊዜ የደረሰበትን ከባድ ችግር በመመልከት ሲገልጽ "የማደርገውን አላውቅም ፤ የምጠላውን አደርገዋለሁና ፤ ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም የማልወደውን የማደርገው ከሆንኩኝ የማደርገው እኔ አይደለሁም በእኔ ላይ አድሮ የሚኖር ኃጢአት ይሠራዋል እንጂ በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛል ፤ ነገር ግን በሰውነቴ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በሰውነቴ ባለኃጢአት የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ ።

ከዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል? እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ በሥጋዬ ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ" ብሏል ሮሜ ፯. ፲፭-፳፭ ።

ሰው ወዶ በፈቃዱ ሳይሆን በሰይጣን ኃይል ተገድዶ ክፉ ሥራ በመሥራት እግዚአብሔርን ይበድላል ። ይሁን እንጂ ሰይጣን ድል ሊያደርገው የሚችለው የፈጣሪውን ትእዛዝ አፍርሶ በራሱ ፍላጐት በተመራ ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ።

ይህንንም በሰፊው ለመረዳት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡትን ታሪኮች መመልከት ይኖርብናል ። በድሮ ዘመን እስራኤላውያን ከኢሉፍላውያን ጋር ስምምነት ስላልነበራቸው ሁልጊዜ ይዋጉ ነበር ። እስራኤላውያን ለጦርነት ሲሰለፉ የእግዚአብሔር ሕግጋት የተጻፉበትን ታቦት እየያዙ ነበር ፤ ሕጉን ጠብቀው ሥነ ሥርዓቱን አክብረው ሲዘምቱ የእግዚአብሔር ኃይል በታቦቱ ላይ አድሮ ስለሚረዳቸው ጠላቶቻቸውን አሸንፈው ሲመለሱ ሕጉን ሳይጠብቁ በዘመቱ ጊዜ ድል ተመተው አፍረው ይመለሱ ነበር ። በዚያም ዘመን ፤

አንድ ኤሊ የሚባል ሊቀ ካህናት ነበር ለ እርሱም አፍኒንና ፊንሃስ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቀው ትእዛዙን አክብረው ለመኖር ባለመቻላቸው አባታቸው ኤሊ ከክፉ ሥራቸው እንዲታረሙ ዘወትር ይመክራቸው ነበር ልጆቹ ግን በተንኮል ላይ ተንኮልን ከመጨመር በስተቀር ከክፉ ሥራቸው ሊታገሡ አልቻሉም ኤሊም ምክሩን እንዳልተቀበሉትና ልዩ ልዩ ኀብረ ኃጢአት መፈጸማቸውን ስለሚሰማ ልጆቼ ወዮላችሁ በማለት ያሳስባቸው ነበር ።

ይህ በዚህ እንዳለ ኢሎፍላውያን እስራኤላውያንን ለመውጋት ጦራቸውን ሰብስበው መጡባቸው እነርሱም የጠላቶቻቸውን መምጣት ስለሰሙ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ለአፍኒንና ፊንሐስ ለካህናቱ ታቦተ እግዚአብሔርን አስይዘው ወደጦሩ ግንባር ተጓዙ በሁለቱ መካከል ጦርነቱ ተጀምሮ ከእስራኤል ወገን ፴ሺ.ህ ሕዝብ አለቁ ። የኤሊ ልጆች አፍኒና ፊንሐስ በጦርነቱ ላይ ሲሞቱ ታቦተ እግዚአብሔርም በኤሎፍላውያን እጅ ተማርካ ተወሰደች ። ከጦር ሜዳ ሸሽቶ ያመለጠ አንድ ሰው እየበረረ ወደኤሊ ሄደ ኤሊ የ98 ዓመት ሽማግሌ ነበርና ወንበሩን ከቤቱ ውጭ አዘርግቶ ተቀምጦ ስለታቦተ ጽዮን ስለ ሕዝበ እስራኤል ስለ ልጆቹ አፍኒና ፊንሐስ ያወጣና ያወርድ ነበርና ያ ከጦር ሜዳ ያመለጠ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ ከጦር ሜዳ መምጣቱን ገለጸለት ኤሊም ሲጨነቅ ነበርና ስለጦርነቱ እንዲያስረዳው በጠየቀው ጊዜ የልጆቹን አፍኒንና ፊንሐስን መሞት የታቦተ ጽዮንን መማረክ ከእስራኤል ወገን ፴ሺ. ሕዝብ ማለቅ ነገረው ኤሊ ሽማግሌ ነበርና ደንግጦ ከወንበሩ በመውደቅ ተሰባብሮ ሞተ ምርዓቱም የፊንሐስ ሚስት እርግዝ ስለነበር ከድንጋጤዋ የተነሣ ምጥ ያዛት ተንበርክካ በምትወልድበት ጊዜ ወደሞትተቃረበች ። በዙሪያዋ የነበሩ ሴቶች ወንድ ልጅ ወልደሻልና አይዞሽ አትደንግጭ አሏት ። እርሷም መልስ አልሰጠቻቸውም ። የእግዚአብሔር ታቦት ስለተማረከች ስለአማቷና ስለ ባሏ መሞት ክብር ከእስራኤል ለቀቀ የእግዚአብሔር ታቦት ተማርካለችና ስትል የሕፃኑን ስም ኢካቦድ ብላ ጠራችው (መ/ሳሙ ቀዳ. ፬.፲፱-፳፪) ።

ኢሎፍላውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ወስደው በሰው አምሳል የተቀረጸውን ጣዖታቸውን ዳጎንን በላይ ታቦተ ጽዮንን በሥር አስቀምጠዋት ሄዱና በበነጋው ለማየት ቢመጡ ዳጎን በታቦተ ጽዮን ፊት በግንባሩ ተደፍቶ አገኙት አሁንም ታቦተ ጽዮንን በሥር ዳጉንን በላይ አድርገው ሄደው በበነጋው መጥተው ቢመለከቱ የዳጎን እጁና እግሩ ተሰባብሮ አገኙትና በጣም ደነገጡ ፤ የአይጥ መንጋም መጥቶ የምድር ፍሬያቸውን ሲያጠፉ በሰዎችም ላይ እባጭ እየወጣ ያሰቃያቸው ጀመር ።

ይህንን ሁሉ ችግር ያመጣችባቸው የእግዚአብሔር ታቦት መሆኗን በመረዳታቸው ወደሀገሯ መልሰው ሰደው በጤና ለመኖር ፈለጉ ። የኤሎፍላውያን ሕዝብ ተሰብስበው ከተመካከሩ በኋላ ለታቦተ ጽዮን ካሣ የሚሆን ወርቅ በማጥን ሞልተው ታቦተ ጽዮንን በሁለት ላሞች ሠረገላ አድርገው የላሞቹን እንቦሶች ለይተው በማስቀረት ወደ እስራኤላውያን ሀገር ላኳቸው ። ላሞቹም ቀኝና ግራ ሳይሉ ወደእስራኤል ሀገር ሲጓዙ የፍልስጥኤማውያን አለቆች በኋላ በኋላ ይከተሏቸው ነበር ። ምድረ እስራኤልም በደረሱ ጊዜ የቤተ ሳሚስ ሰዎች የታቦተ ጽዮንን መምጣት አይተው በጣም ደስ ብሏቸው ተቀብለዋታል ። ተቀብለውም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አቅርበዋል መ/ሳሙ ቀዳ. ፮.፲፮።

የታቦተ ጽዮን ኃይል አሁንም እየጨመረ ሥራ ይሠራል እንጂ አልተቀነሠም በተመለከትነው ታሪክ ጠቃሚዎች የሆኑ ቁም ነገሮችን ለመቅሰም እንችላለን ።

አንደኛ የአፍኒንና ፊንሃስን ሁኔታ ስንመለከት የአባትን ምክር አለመስማት ከእንዴት ያለ ጥፋት ላይ እንደሚጥል ለመረዳት እንችላለን የኤሊ ልጆች ክፋታቸውን ተንኮላቸውን እንዲተው አባታቸው መላልሶ መከሯቸው ነበር ነገር ግን ምክሩን ንቀው ባለመቀበላቸው እንደተቀሠፉ ተመልክተናል ። የጠፉትም ብቻቸውን አይደለም ለአባታቸው ለኤሊና ለ፴ሺ.ህ ሕዝብ ሞት ምክንያቶች የሆኑት እነርሱ ናቸው ።

"የኃጥእ ዳፋ ጻድቁን ያዳፋ" እንደሚባለው በተንኮለኞች ሰዎች ምክንያት የሚታዘዘው መቅሠፍት ደጋጐችንም እንደሚያጠፋቸው አይጠረጠርም ።

ሁለተኛ ታቦት ማለት የእግዚአብሔር ቃል ማደሪያ ማለት ነው በክርስቶስ የሚያምኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ታቦተ እግዚአብሔር ይባላሉ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሚባሉ ክርስቲያኖች ደግሞ ሰውነታቸውን ከኃጢአት ከበደል ከክፉ ሥራ መለየት ያስፈልጋቸዋል ። ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን ግንኙነት አለው እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና ይላል ፪ኛ ቆሮ ፮.፲፮ ።

ይኸው ሐዋርያ በተጨማሪ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔር መንፈስ አድሮባችሁ እንደሚኖር አታውቁምን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ ብሏል ፩ኛ ቆሮ ፫. ፲፯ ።

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች የምንባል በክርስቶስ ስም አምነን የተጠመቅን ሁላችን መሆናችን ተገንዝበን በፍጹም ልባችን ክርስቶስን መከተል ይገባናል የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነውን ሰውነታችን የሰይጣን ማደሪያ ማድረግ አይገባንም ።

ታቦተ እግዚአብሔር ጽዮን ዳጎን የሚባለውን የኢሎፍላውያንን ጣዖት ቆራርጣ እንደጣለችው ተመልክተናል የእኛም ሰውነት በታቦት ተመስሏል ። በታቦት የተመሰለው ሰውነታችን የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት በመሆኑ ሰይጣን ድል ሊያደርገው አይችልም ሰይጣንን አሸንፎ የማባረር ኃይል አለውና ነገር ግን ሰውነታችን ለሰይጣን ሊሸነፍ የሚችለው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፍርሰን የማይገባ ሥራ ሥንሠራ ነው ስለዚህ የማይገባ ሥራ ሠርተን የሰይጣን ተገዥዎች ከመሆን እንድን ዘንድ አምላካችን በቸርነቱ ይርዳን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ዘመነ ሚጠት

ዘመነ ሚጠት የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ነው ትርጉሙ የመመለስ ዘመን ማለት ነው ። ስለዚህ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በግብሩ ጥበብ ይለዋል የባህርይ ጥበቡን ለሰው የሚገልጽለት ስለሆነ ነው ማስረጃውም እንዲህ ይላል ጥበብ እግዚአብሔርን ከዘነት ከሰባ ሰዶም ከሰባ ገሞራ ለይታ ሎጥን አዳነችው ። በአምስቱ አህጉር ላይ እሳት በወረደች ጊዜ እስከ ሴጥር ድረስ በመሸሽ አዳነችው አምስት አህጉር የተባሉትም ሶዶም ገሞራ አዳማ ሱባማ ሲባዮን ናቸው ዘፍጥረት ፲፱. ፩-፳፭ ይችም ጥበብ ከወንድሙ ቁጣ የተነሣ የሸሸ ያዕቆብን ወደ ቀና መንገድ መራች ይላል ዘፍጥረት ፳፰.፩-፲፱ ።

በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ለሎጥ የመሸሽን ጥበብና ዘዴ ባይገልጽለት በሰዶምና በገሞራ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር በእሳት ተቃጥሎ በሞተ ነበር ። ያዕቆብንም ከወንድሙ ከኤሣው ቁጣ የተነሣ ሸሽቶ የሚያመልጥበት ጥበብን ባይገልጽለት ወንድሙ ኤሣው በገደለው ነበር ። ስለዚህም ከማይቻል ጠላት ሸሽቶና ተሰዶ መዳን ከእግዚአብሔር የተገኘ ጥበብ ነው እንጂ መፍራት አይደለም ። እንዲሁም ዓክአብ ኤልያስ ይህን ሁሉ እንዲያደርግ ነቢያትም ሁሉ በሰይፍ እንደገደለ ለኤልዛቤል ነገራት ኤልዛቤልም ከዚህ ጊዜ ነፍስህን ከነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደረጋት አማልክት ይህን ያድርጉብኝ ይህንንም ይጨምሩብኝ ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች ኤልያስም ፈጥኖ ተነሣ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ ደግሞም እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና ሌሊት ሄደ ይላል (አንደኛ ነገሥት ፲፱.፲፰) እንዲሁም ደግሞ በሐዲስ ኪዳን እንዲህ የሚል ይገኛል እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ሔሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ምስር ግብጽ ሽሽ እስከ ነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው እሱም ተነስቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢዩ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ (ማቴዎስ ፪.፲፫-፲፭) በዚያም ጊዜ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇዋን ይዛ ከአንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ስትሸሽ የፀሐይ ሐሩር የሌሊት ቁር እያቃጠላት በተጨማሪም በእግር ስትጓዝ እንቅፋት እየመታት እሾህ እየወጋት እራብና ጥም መከራና ድካም ደርሶባታል ።

አንዳንድ ጊዜም የሄሮድስ መልእክተኞች በኋላ እየተከተሉ ሲያሳድዷት እንዲሁም በበርሀ ስትሄድ ሽፍቶችን ባየች ጊዜ የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር የተቀበልኩት ልጄን ከሞት ላላድን ነውን ? እያለች ስታለቅስ እንባዋም በምትወደው በልጅዋ ፊት ላይ በዝቶ ይወርድ ነበር ስለዚህም ይህንን ሁሉ ፀዋትወ መከራ በመታገስዋ የሰማዕታት እናት ተብላለች ስደትን ባርካ የሰጠችቸው እሷ ናትና ሰማዕትነትም እሳትና ስለት መቀበል ብቻ አይደለም ስለሃይማኖት ብሎ መሰደድም ሰማዕትነት ነው ።

ከዚህም ላይ ልናስተውለው የሚገባ ዓቢይ ነገር አለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የአምላክ እናት ስትሆን በዚህ ዓለም በስደትና በመከራ ኖረች እንጂ በተድላና በደስታ አልኖረችም።ጌታም በአምላክነቱ ፍርሃትና ሞት የማይስማማው ሁሉንም ማድረግ የሚችል ሲሆን ከልደት እስከ ስቅለት ድረስ ብዙ መከራ ተቀብሎ ሙቶ ተሰቅሎ ዓለምን አዳነ እንጂ በምን እዳየ ነው አላለም በደስታ መኖርንም አልፈቀደም ለምን ቢባል ለትዕግሥት አርአያ ምሳሌ ለመሆን ነው ። ስለዚህ መከራ አይንካኝ የሚል ሰው ቢኖር ከጌታው የሚበልጥ ሎሌ ከመምህሩ የሚበልጥ ደቀ መዝሙር የለም የሚለውን ቃለ ወንጌል ያስተውል (የሐ ፲፫-፲፮) ከዚህ ቀጥሎ ዘመነ ሚጠት ተብሎ በርእሱ የተነገረውን ማወቅ ይገባል ።

ዘመነ ሚጠት ከስደት መመለስ እንደሆነ በመጀመሪያ ተገልጿል ። እርሱም እንደሚከተለው ነው ። ሄሮድስም ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሙተዋልና ተነሣ እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለው እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑን እናቱንም ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ በዚህም እመቤታችን ድንግል ማርያምን ጌታን ይዛ ስለተመለሰች ልጄን ከግብፅ ጠራሁት ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጽሟል ይሁን እንጂ ምድረ እስራኤል ከመግባቷ በፊት ከስደት ተመልሣ ከብዙ ድካም ያረፈችበት ቦታ ደብረ ቁስቋም ይባላል ስለሆነም የእመቤታችን የልደቷና የመመለሷ መታሰቢያ ሁኖ በየዓመቱ ኅዳር በባተ በ፮ ቀን እጅግ በደመቀ ሁኔታ ይከበራል ። ደብረ ቁስቋም ከድካም ያረፈችበት ጌታን ይዛ የአደረችበት ስለሆነ የተባረከና የተቀደሰ ቦታ ነው ። በኋላም በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል ጌታም በዚሁ ቦታ ተገልጾ ሐዋርያትን ከያሉበት አምጥቶ ከእነርሱ ጋር ቀድሶ ሥጋውንና ደሙን ለምዕመናን አድሎ ሲፈጽም ባርኮአቸው ወደ ሰማይ እንዳረገ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይናገራል።ከዚያም ወዲህ እመቤታችን ከልጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እየታየች በዚያ የተሰበሰቡትን ምዕመናን ስትባርካቸው እንጦስ የሚባል የበቃ ደግ ሰው አይቶ ተናግሯል ። እኛም በልጅዋ አምነን፣ በቃልኪዳኗ ተማጽነን ለመባረክ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን አሜን ።

መ/ይባቤ መላክ



# አርባዕቱ እንስሳ ፡

አርባዕቱ እንስሳ በሌላም አጠራር ኪሩቤል ወይም ሱራፌል ይባላሉ ። ቁጥራቸው ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ሲሆን የእግዚአብሔርን መንበር ተሸክመው የሚኖሩ ረቂቃን መላእክት ናቸው ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ያየውን እንደተናገረው "ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት ። የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር ፣ ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር ፣ ለእያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች ነበሩዋቸው ፣ በሁለት ክንፎቻቸው ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር ። በሁለት ክንፎቻቸው ወደ አንድ አቅጣጫ ይበሩ ነበር ። ሁሉም በአንድ ቃል ቅዱስ ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና ሰማይና ምድርን የሞላ ነው ። እያሉ ያመሰግናሉ ብሏል ። ኢሳ ፮፣፩-፫ ።

ይህም በሊቃውንቱ ሲተረጐም ሁለት ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ፊታቸውን መሸፈናቸው ወደላይ ቢወጡ ቢወጡ የማትመረመር አምላክ ነህ ሲሉ ነው ፤ ሁለት ክንፎቻቸውን ወደ ታች ዘርግተው እግሮቻቸውን መሸፈናቸው ወደታች ቢወርዱ ቢወርዱ የማትመረመር ነህ አ ማለታቸው ሲሆን ፣ ሁለት ክንፎቻቸውን ዘርግተው እየበረሩ መታየታቸው ደግሞ በዓለም ላይ ወሰን የሌለህ ምሉዕ በኩልሄ ነህ ሲሉ መሆኑን ይገልጻሉ ።

አርባዕቱ እንስሳ ስማቸው እንደሚያመለክተው በአራት የእንስሳት መልክ የተከፋፈሉ ሆነው ፩ኛው በሰው መልክ ፣ ፪ኛው በአንበሳ ፣ ፫ኛ በላም ፣ ፬ኛው በአሞራ ይመስላሉ በእንስሶቹም መካከል እንደሚነድ የእሳት ፍም ያለ ምስያ ነበረ ። በዚያም ወዲያና ወዲህ የሚሄድ እንደፋና ያለ አምሳያ ነበረ ፣ ለእሳቱም ፀዳል ነበረው ከእሳቱም መብረቅ ይወጣ ነበር" በማለት ነቢዩ ሕዝቅኤልም ያየውን ይናገራል ። ሕዝ ፮ ፣ ፲፫ ፣

የሰው ምሳሌ ያለው ኪሩብ ለሰው ልጆች ምሕረትን ሲለምን ፣ ሲያማልድና ሲጸልይ ይኖራል ። የአንበሳ ምሳሌ ያለውም ለዱር አራዊት ከሚደርስባቸው ሕልቂት እንዲድኑ ይጸልያል ። የላም ምሳሌ ያለውም ለቤት እንስሳት እንደድርቅና ልዩ ልዩ በሽታዎች ያሉት እንዳይደርሱባቸው ሲጸልይ ይኖራል ። የአሞራ ምሳሌ ያለው ደግሞ ለአእዋፍ ሁሉ እየጸለየ ሲጠብቅ የሚኖር መሆኑን ይገልጻል ።

ወንጌላዊው ዮሐንስም በራዕዩ ለኢሳይያስና ለሕዝቅኤል ከታያቸው የተለየ ሳይሆን ያየውን በማብራራት እንደሚከተለው ይገልጻል ። በመንበሩ ላይ ተቀምጦ ያየሁት ኅብሩ የኢያስጴድንና የሰርዲኖንን ዕንቁ ይመስላል ካለ በኋላ አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉዋቸው ። በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዐይኖች ሞልተውባቸዋል ። ሃሌ ሉያ ቅድመ ዓለም የነበረው ፣ አሁንም ያለው ፣ ወደፊትም የሚኖረውና ሁሉንም የሚችል አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት ያለማቋረጥ ያመሰግኑታል ። ሃያ አራቱም ካህናተ ሰማይ በፊቱ እየሰገዱ ያመሰግኑታል ። በማለት ያብራራል ራዕ ፬ ፣ ፰-፲ ።

በነዚህም በአርባዕቱ ኪሩቤል አርባዕቱ ወንጌላውያን ተመስለዋል በገጸ ሰብእ ምሳሌ ማቴዎስ ፣ በገጸ አንበሳ ምሳሌ ማርቆስ ፣ በገጸ ላህም ሉቃስ ፣ በገጸ ንስር ምሳሌም ዮሐንስ ሲሆኑ ፣ ዘብእሲ ማቴዎስ፣ ዘአንበሳ ማርቆስ ፣ ዘላሕም ሉቃስ ፣ ዘንስር ዮሐንስ በመባል ይጠራሉ ።

አራቱም ኪሩቤል እያንዳንዳቸው ፊታቸውን ወደ አራቱ ማዕዘናት አድርገው ሲያመሰግኑ ይኖራሉ እንጂ እርስ በእርሳቸው (ፊት ለፊት) አይተያዩም። ይህም ሲሆን ሁሉም ወደ የፊታቸው አያመሩም እንደሰው እረፍተ ሥጋ ምግበ ሥጋ ስለማያስፈልጋቸው ድካምና እንቅልፍም ስለሌለባቸው እግዚአብሔርን ለዘለዓለም ሲያመሰግኑ ይኖራሉ ።

የእግዚአብሔር ሕልውናና ግርማ መለኮት በዚህ ዓይነት ይገለጽ እንጂ ኪሩቤል በተሸከሙት መንበር ላይ ብቻ ተወስኖ ይኖራል ማለት አይደለም ። ኪሩቤልን የሚሸከም ፣ ዓለማትን በመሐል እጅ የያዘ ፣ የትም ቦታ ያለ ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ነው ።

ነቢያትም ሆኑ ሌሎች ቅዱሳን በዐይናቸው ያዩትን በጆሮአቸው የሰሙትን ከእርሱም የተቀበሉትን ሕግ መስክረው አስተምረውና ጽፈው ለትውልድ አስረክበው አለፉ እንጂ ማናቸውም ፍጡር ቢሆን የአምላክነቱን ምልአትና ስፋት ምጥቀትና ርቀት መርምሮ የደረሰበት የለም አሁንም ያለነው ብንሆን ያየነውንና የሰማነውን ላላዩትና ላልሰሙት መመስከር ፣ የተማርነውንም ላልተማሩት ማስተማር ፣ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ለትውልድ ማስተላለፍ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው እንጂ ከምናውቀውና ከምንችለው በላይ የሆነውን የአምላክነትን ሥራ መርምሮ መድረስ አንችልም ። ስለዚህ በተቻለን እናመስግናለን በተቻለንም እናስተምራለን ።

እግዚአብሔር ለምስጋና መላእክትን ብቻ ፈጥሮ አልቀረም ሰውንም በሕጉ ጸንቶ እንዲኖርና እንዲያመሰግነው ኋላም የክብሩ ወራሽ እንዲሆን አክብሮ በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮታል ። ስለዚህ እንደመላእክት ያለ ምስጋና ማቅረብ ባንችልም ጧትም ሆነ ማታ የሰማይ አባታችን ሆይ "ብለን ስሙን በመጥራት ማመስገን ይገባናል ። ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ አብልጦ አዋቂ በማድረግ የፈጠረን የሰው ልጆች ቀርቶ



www.ethiopianorthodox.org

አራዊትና እንስሳት እንኳን በተሰጣቸው ዕውቀትና አእምሮ ያመሰግኑታል እነሱም ይቅሩና አእምሮ ገዕዛን የሌላቸው አዕባን ፣ እንኳ ሳይቀሩ አመስግነውታል ።

ለምሳሌ በደብረ ታቦር በተገለጸበት ጊዜ ተራሮች እንደሰገዱለት ፣ በፈለገ ዮርዳኖስም በተጠመቀ ጊዜ ባሕር እንደሸሸች ውሆች እንደተሸበሩ ፣ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ ብርሃኗን እንደከለከለች፣ ጨረቃ ደም እንደለበሰች ከዋክብትም እንደረገፉ በዐይነ ልቡና ስንመለከት ከእኛማ የቱን ያህል እንደሚፈለግብን ማሰብ አያዳግተንም ።

ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት መሣሪያ ፣ ጊዜና ኅብረት ያስፈልጋሉ ። ሠራተኞችም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን መሣሪያዎች ይዘው ሰዓት አክብረው በኅብረት ከሠሩ የሥራቸው ውጤት ያማረ የሠመረ ይሆናል ። ለምስጋናም የተወሰነ ሰዓት ፣ የተለያዩ መሣሪያዎችና አንድነት ያላቸው ትጉሃን አመስጋኞች ያስፈልጋሉ ። ለምሳሌ በመላእክት የተመሰሉ ካህናት በሰዓት ተገኝተው እንደከበሮ ጸናጽልና ቃጭል ባሉት መሣሪያዎች በአንድ ድምፅ እግዚአብሔርን ስለድንቅ ሥራው ሲያመሰግኑ ፣ ስለ ዓለም ድኅነት ሲጸልዩ ንጹሕ መሥዋዕትን ሲያቀርቡ ፣ ምሥጋናቸው ደርሶ ፣ ጸሎታቸው ተሰምቶ ፣ መሥዋዕታቸው ሠምሮ ፣ ሀገርንና ወገንን የሚጠብቅ ከፈጣሪ የሚያማልድ ፣ ከሚመጣው መቅሰፍት እንደረሐብ ፣ በሽታና ድርቅ ከመሳሰሉት አሰቃቂ ነገሮች ሁሉ የሚከላከል ይሆናል ።

ሌላው ደግሞ ሴት ወንድ ልጅ አዋቂ ፣ የተማረ ያልተማረ ሳይባል ሁሉም እንደችሎታው በአመቸው ሰዓት በግል የሚቀርብ ምስጋናና ጸሎት ነው ። ይህም ለአምላክ ታላቅ ግንዘቡ ስለሆነ ጧትም ሆነ ማታ ፣ ሌሊትም ሆነ ቀን ፣ በማኅበርም ሆነ በግል ቢቀርብለት ይቀበላል ።

ማንኛውም አማኝ በቅድሚያ ማድረግ የሚገባው ባለፈው ስለተደረገለት ቸሮታ ማመስገን በጊዜው ም ያለበትን ጉድለት እንዲያሟላለትና ለወደፊቱም ከሚደርሰው ክፉ ነገር እንዲጠብቀው ከልብ መጸለይ ነው ። ምስጋና በሰውም ዘንድ ታላቅ ዋጋ ያለው መሆኑ ግልጽ ነው ። አንዱ ለሌላው ስለአደረገለት ቁም ነገር ደስ ብሎት ሲያመሰግነው ተቀባዩም ደስ ይለዋል ። እንደዚሁም ክርስቶስ ለኛ ያደረገውን ታላቅ ቸርነት ስለእኛም የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ እያሰብን ስናመሰግነው ደስ ብሎት ይቀበለናል ። ባናመሰግነው ግን እኛ ምስጋና቟ ቢሶች ሆነን የሚገባንን ክብር እናጣለን እንጂ ለእርሱ የሚጐድልበት ነገር የለም ።

ፍጹም እምነት ያለን ሕገ እግዚአብሔርን የማንጥስ ዘወትር እሱን እያመሰገንን የምንኖር ከሆነ ፣ የሚችለን እሱ ቢሆንም እንደኪሩቤል እግዚአብሔርን እያመሰገንን ብንኖር በሕይወተ ሥጋም ሆነ በሕይወተ ነፍስ ችግርና ጨለማ የለብንም በብርሃን እንመላለሳለን ። እሱ ራሱ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ። የሚከተለኝ ሁሉ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ”ሲል ቃል ገብቶልናል ። ዮሐ ፰፥፲፪ ፣

ቤተ ክርስቲያናችንም እንደደነገገችው የነዚህ ግሩማን መላእክት አርባዕቱ እንስሳ መታሰቢያ በዓል የሚከበረው ኅዳር ፰ ቀን በየዓመቱ ስለሆነ በዚሁ ዕለት ታቦታቸው ወደአለበት ቦታ እየሄድን ብናከብርና መታሰቢያቸውንም ብናደርግ ቅሩባነ አምላክ እንደ መሆናቸው መጠን በረከታቸውና አማላጅነታቸው የማይለየን መሆኑን እንዘንጋ ።

መ/መንክር ዋሴ

# የአዋሳ ካህናት.....

ከገጽ ፩ የዞረ

የብርሃንን ጥቅም ታውቃላችሁ ብርሃን ከዕንቅብ በታች ወይም ከጋን ውስጥ አብርተው ቢደብቁት ብርሃኑ ምንም ጥቅም እንደሌለው ታውቃላችሁ በከፍተኛ ቦታና በአመች ሥፍራ ቢያስቀምጡት ግን ለሁሉም ጥሩ ጥቅም ይሰጣል ስለዚህ የካህናት መልካም ሥራ በብርሃን ይመሰላል የካህናት ክፉ ሥራ ደግሞ እንደተደበቀ መብራት ነው ።

እንዲሁም ጨው ጨውነቱ የሚታወቀው ጣዕም ሲሰጥ ነው ። አለዚያ ከሚረገጠውና ወዲያ ከሚጣለው ድንጋይ እኩል ነው ስለዚህ እንደ ጨው ትመሰገኑ ዘንድ ለክህነት ተጠርታችኋል ክህነታችሁም ታዋቂና ተወዳጅ እንዲሆን የአባቶቻችሁን የሐዋርያትን አርአያ ጠብቃችሁ የተጣለባችሁን አደራ በትጋት እንድትወጡ ይገባችኋል የሚል ይገኝበታል ሲሉ መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው ገልጸዋል ።

መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው በማሠልጠኛው ስለቆዩት ደቀ መዛሙርት ተግባር ሲያትቱ ተማሪዎች በተሠጣቸው ፕሮግራም መሠረት በማሠልጠኛው ውስጥ በሚገኘው የልማት መሬት ላይ 1000 የፍራ ፍሬና ልዩ ልዩ ዛፎች ዘንባባ ቡና ኮሸም ቁንዶ በርበሬ በድምሩ ፲ሺህ (አሥራ ሺህ) ያህል ዙሪያውን በተክል አሸብርቀውበታል ብለዋል።

እንዲሁም ፯፻፶ ጉድጓድ ሸንኮራ ፱፻ እግር ሙዝ ፩፻ ፓፓያ አልምተው በቆሎውንም አዝምረው አርመውና ኮትኩተው ለ፭፻ኛው ዙር በጥሩ ሁኔታ አስተላልፈዋል በትምህርታቸው ጊዜም በወርና በዓበይት በዓላት በአዋሳ አካባቢ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት እየ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



# መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በፊታቸው ይሔዳል

መቅደምና መከተል የተለያዩ ዓላማዎች አሏቸው አንደኛው የአክብሮትና የትሕትና ሲሆን ሁለተኛው የአቀባበል ዝግጅት ነው ለምሳሌ ለግብዣ የተጠሩ ሰዎች አብረው በሚሄዱበት ጊዜና በሚቀመጡበት ሰዓት አንተ በፊት ሂድ አንተ በፊት ተቀመጥ በመባባል ይገባበዛሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ሩቅ ሀገር ለመሔድ የሚፈልጉና አንድ ታላቅ ዝግጅት ለማድረግ ያሰቡ ሰዎች አስቀድመው መልእክተኞቹን በመላክ ጉዳዩ እንዲሠምር ያደርጋሉ ።

ለማስረጃ ይሆነን ዘንድ ቅዱስ መጽሐፍን እንመልከት ጌታችን መሥዋዕተ ኦሪትን አሳልፎ መሥዋዕተ ወንጌልን ከመተካቱ በፊት ጴጥሮስንና ዮሐንስን ፋሲካን እንድንበላ በፊት እናንተ ሂዱ ችሁ አዘጋጁልን ብሎ ላካቸው እነርሱም ወዴት እናዘጋጅ ዘንድ ትወዳለህ ? አሉት እርሱም እነሆ ወደከተማ ስትገቡ ማድጋ ውሃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል ወደሚገባበት ቤት ተከተሉት ለባለቤቱም መምህር ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ክፍል ወዴት ነው ? ይልሃል በሉት ያም በደርብ ላይ ያለውን የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል በዚያም አሰናዱልኝ አላቸው ሂደውም እንዳላቸው አገኙና ፋሲካን አዘጋጁ ሉቃስ ፳፪፥፰-፲፫

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በቅድሚያ ወደ ተዘጋጀው ቤት በደቀመዛሙርቱ ጋር ገብተው ከተመገቡ በኋላ መሥዋዕተ ኦሪትን አሳልፎ መሥዋዕተ ወንጌልን ተክቶላቸዋል ፤ እንዲሁም በአህያ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ከመግባቱ በፊት ሁለት ደቀ መዛሙርትን አህያ ከውርንጫዋ ጋር እንዲያመጡለት ልኮ ካመጡለት በኋላ በአህያይቱ ላይ ተቀምጦ በፊቱ አዕሩግና ሕፃናት እየሄዱ በማመስገን ወደቤተ መቅደስ ሂዶ በቤተ መቅደስ አካባቢ ይፈጸም የነበረውን የማይገባ ሥራ አስወግዶ ዘመነ ሰላም መድረሱን ለሕዝቡ አብሥሯቸዋል ማቴ. ፳፩-፩-፭ ።

በተጨማሪም አንድ ዘኬዎስ የሚባል ባለጸጋ ክርስቶስን ለማየት ይፈልግ ስለነበር የሚሄድበትን መንገድ ጠይቆ አስቀድሞ ሄደና ከዛፍ ላይ ወጥቶ ሲጠብቅ ክርስቶስ በቅድሚያ ስላየው ከዛፉ ላይ ፈጥኖ ወርዶ ወደቤቱ በመሄድ ግብዣ እንዲያሰናዳ አዘዘው እርሱም ትእዛዙን ተቀብሎ ግብዣውን አዘጋጀለት ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሄዶ ሲጋበዝ ዘኬዎስ ቆሞ ጌታ ሆይ! ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆነ አራት እጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ አለው ክርስቶስም ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሁኖለታል የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግ የተጐዳውን ሊያድን ሰው ሁኖአልና በማለት ምኞቱን ፈጽሞለታል ሉቃስ ፲፱፥፭

በፊት ቀድመው የሚሠሩ ተግባሮች እንደእነዚህ የመሰሉ ናቸው በዚህ አንጻር ለመግለጽ የፈለግነው ኅዳር ፲፪ ቀን ስለሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል ዓመታዊ በዓል ነው በዚህ ዕለት የእግዚአብሔርን ቸርነት የቅዱስ ሚካኤልን ተራዳኢነት በሰፊው ለመረዳት የምንችልበትን አስደናቂ ሥራ ለመመልከት እንችላለን ።

ሕዝበ እስራኤል በረኀብ ምክንያት ወደ ግብፅ ተሰድደው 430 ዓመታት ኑረዋል በዚያም ሲኖሩ ግብፃውያን ይጨቁኗቸው ና ይጠሏቸው ነበር ከጥላቻቸው የተነሣ ከባድ ከባዱን ሥራ እንዲሠሩ የሚመደቡት እነርሱ ብቻ ነበሩ ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከእስራኤል ወገን የሆነችው ራሄል ኖራ እንድትረግጥ ታዝዛ ስትረግጥ ምጥ ተሰማት ምጥ ተሰማኝ እባክህ አሳርፈኝ ብላ አሠሪውን ብትጠይቀው አይሆንም አላት ወዲያው መንታ ፀንሳ ነበርና ሁለት ሕፃናት ከማኅፀኗ ወጥተው ስለወደቁ ደንግጣ ቆመች ምን ያስደነግጥሻል የሰው ደም ኖራውን ያጠብቀዋል እንጂ ምን ይለዋል በይ ጨምረሽ እርገጫቸው ብሎ መታት ጨምራ ረገጠቻቸው “ኢሀሎኑ በዝ ሰማይ አምላክ እስራኤል አዶናይ” ብላ እንባዋን ወደ ላይ ብትረጨው ቅድመ እግዚአብሔር ደርሷል ጌታንም “ርእየ ርኢኩ ሕማሞሙ ለሕዝብየ ወሰማዕኩ ገዓሮሙ ወወረድኩ ከመ አድኅኖሙ” የሕዝቡን ጩኸት ሰምቼ ላድናቸው መጣሁ ያሰኘው ይህ የራሄል እንባ ነው ኦር ፴፩፥፲፭ ።

እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ ለማውጣት በፈቀደ ጊዜ ከመካከላቸው ሙሴን አሥነሣና ወደፈርዖን ላከው ሙሴም እስራኤልን እንዲለቅ ለፈርዖን ቢነግረው እግዚአብሔርን አላውቅም ባሮችን እስራኤልንም አልለቅም ብሎ ተናገረ በእንቢተኛነቱና ለፈጣሪው አልታዘዝም በማለቱ

፩ኛ/ የወንዙ ውሀ ሁሉ ተለውጦ ደም ሆነ

፪ኛ/ ጓጉንቸሮች ወጥተው የግብጽን ምድር ሸፈኑት

፫ኛ/ በሰውና በእንስሳ ላይ ቅማል ሆነ

፬ኛ/ ተቆናጣጭ ዝንብ መጥቶ ሰውንና እንስሳውን አሠቃየው

፭ኛ/ የግብፃውያንን ከብቶች ተኽር ፈጃቸው

፮ኛ/ በሰውና በእንስሳ ላይ ቁስል እየወጣ አሰቃያቸው



www.ethiopianorthodox.org

፯ኛ/ ታላቅና ከባድ በረዶ እሳት የተቀላ
ቀለበት ወርዶ ወይናቸውንና አትክል
ታቸውን ሰውንና እንስሳውን ጐዳባ
ቸው

፰ኛ/ አንበጣ መጥቶ ምድራቸውን ሸፈ
ናት ከበረዶ የተረፈውንም ፍሬ ሁሉ አ
ጠፋባቸው

፱ኛ/ ሦስት ቀን ሙሉ በግብጽ ጨለማ
ሆነ

፲ኛ/ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ
በኩር በኩሩ ሞተ ይህ ሁሉ ሲሆን እየ
ተመለከተ ፈርዖን የእግዚአብሔርን ት
እዛዝ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኖ አልተገ
ኘም_ለጊዜው እስራኤላውያን ከምድረ
ግብፅ በአስቸኳይ ወጥተው እንዲሄዱ
ቢያዝዝም እነርሱ ወጥተው የግብፅ ከ
ተማ ጭር ማለቷን በተመለከተ ጊዜ
ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት ብሎ እስ
ራኤላውያንን መልሶ ባሮች አድርጐ ለ
መግዛት ይከተላቸው ጀመር ።

ቅዱስ ሚካኤል እስራኤላውያንን እ
የመራ በፊት በፊታቸው ይሄድ ነበር ፈ
ርዖን ከእነሠራዊቱ እየገሠገሠ ወደ ሕ
ዝበ እስራኤል ሲቃረብ እስራኤላውያን
ተመልክተው እጅግ በጣም ፈሩ ወደ
እግዚአብሔርም ጮሁ ሙሴንም ለም
ን ከግብፅ አወጣኸን በምድረ በዳ ከም
ንቀር ለፈርዖን ባሪያዎች ሆነን ብንገዛ
ይሻለን ነበር እያሉ በሙሴ ላይ አጉረመ
ረሙ ።

ሙሴም ለሕዝቡ አይዟችሁ አትፍሩ
ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን ለዘ
ለዓለም አታዩአቸውምና ቁሙ ዛሬ ለእ
ናንተ የሚያደርግላችሁን የእግዚአብሔ
ርን ማዳን እዩ እግዚአብሔር ስለእናንተ
ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ አላ
ቸው ወዲያው እግዚአብሔር አምላክ
ሙሴን ለምን ትጮሃላችሁ እንዲጓዙ
ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አንተም
በትርህን አንሣ እጅህንም በባሕሩ ላይ
ዘርጋ ክፈለውም የእስራኤልም ልጆች
በባሕሩ ውስጥ በደረቅ ያልፋሉ እነሆ
እኔም የግብፃውያንን ልብ አጸናለሁ በ
ኋላቸውም ይገባሉ በፈርዖንና በሠራዊ
ቱም ሁሉ በሠረገሎቹም በፈረሶቹም
ላይ ክብር አገኛለሁ አሰጥማቸዋለሁም
ያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ
ኝ ያውቃሉ አለው ።

በእስራኤል ሠራዊት ፊት ይሄድ የነ
በረው መልአኩ ቅ/ሚካኤል ፈቀቅ ብሎ
በስተኋላቸው ይሄድ ጀመር የደመናው
ም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ በኋ
ላቸው ቆመ በግብፃውያን ሰፈርና በእስ
ራኤል ሠፈር መካከል ገባ በዚያም ደመ
ናና ጨለማ ነበር በእስራኤል በኩል ግን
ብርሃን ነበር ቢሆንም ግብፃውያንና እስ
ራኤላውያን አልተቃረቡም ለመተያየ
ትም አልቻሉም ።

ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ እግ
ዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥ
ራቅ ነፋስን አምጥቶ ባሕሩን አደረቀው
የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል
በየብስ ገቡ ፣ ውኃውም በቀኛቸውና በ
ግራቸው እንደግድግዳ ሆነላቸው ፤ግብ
ፃውያንም የፈርዖን ፈረሶችና ሠረገሎች
ፈረሰኞችም ሁሉ እያሳደዱ በኋላቸው
ወደ ባሕሩ መካከል ገቡ ንጋትም በሆነ
ጊዜ እግዚአብሔር በእሳትና በደመና
ዓምድ ሆኖ የግብፃውያንን ሠራዊት ተ
መለከተ የግብፃውያንንም ሠራዊት አ
ወከ የሠረገሎቹንም መንኰራኩር አሰረ
ወደጭንቅም አገባቸው ግብፃውያንም
እግዚአብሔር ይዋጋላቸዋልና ከእስራ
ኤል ፊት እንሽሽ አሉ ግን ሸሽተው ለ
ማምለጥ አልቻሉም እግዚአብሔርም
ሙሴን ባሕሩን በበትሩ እንዲመታው ስ
ላዘዘው ባሕሩን በበትሩ በመታው ጊዜ
ባሕሩ ተመልሶ ስለገጠመ ግብፃውያንን
ከእነፈረሶቻቸው ከእነሠረገሎቻቸው
አስጥሟቸዋል ከመካከላቸው ለወሬ ነ
ጋሪ አልቀረም ።

ለእስራኤላውያን ግን ባሕሩ በቀኝና
በግራ በላይ በታች ተከፍሎ እንደግድግ
ዳ ስለሆነላቸው ከመካከላቸው አንድ
ሰው ሳይጠፋ ተሻገሩ እግዚአብሔር
በዚያ ቀን እስራኤልን ከግብፃውያን
እጅ አዳነ እስራኤልም የግብፃውያንን
ስጥመት በባሕር ላይ ለማየት ቻሉ እግ
ዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያደረጋት
ን ታላቂቱን እጅም አዩ ሕዝቡም እግ
ዚአብሔርን ፈሩ በእግዚአብሔርም አ
መኑ -ዘፀ.፲፬፡፴፩)

እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን
ቸርነትና አዳኝነት የመላኩን ቅ/ሚካኤ
ል ተራዳኢነት አምነው በጽንፈ ኤርት
ራ ዘምረዋል የመዝሙሩም ኃይለ ቃል
"እግዚአብሔር ተዋጊ ነው ስሙ እግዚ
አብሔር ነው የፈርዖንን ሠረገሎች ሠ
ራዊቱንም በባሕር ጣላቸው የተመረጡ
ት ሦስተኞች በኤርትራ ባሕር ሰጠሙ
ቀላያትም ከደኑአቸው ወደባሕር ጥል
ቀት እንደደንጊያ ሰጠሙ አቤቱ ቀኝህ
ጠላቱን አደቀቀ በባህርም ብዛት የተነ
ሡብህን አጠፋህ ቁጣህን ሰደድህ እን
ደገለባም በላቸው በአፍንጫህ እስትን
ፋስ ውሆች ተከመሩ ፈሳሾችም እንደ
ክምር ቆሙ ሞገዱም በባሕር ውስጥ
ረጋ ።

የፈርዖን ፈረሶች ከሠረገሎቹም ከፈ
ረሰኞቹም ጋር ወደ ባሕር ገቡ እግዚአ
ብሔርም የባሕሩን ውሆች መለሰባቸው
የእስራኤል ልጆች ግን በባሕሩ መካከል
በየብስ ተሻገሩ የሚል ነው ።(ዘፀ ፲፭.
፫-፲፱) ።

ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ከም
ድረ ግብፅ ከወጡ በኋላ ፈጣሪያቸውን
በማማረራቸው በ40 ቀን ይደረስ የነበ
ረው ቦታ 40 ዓመት እንደሚያስኬድ
ሆኖባቸዋል ።

በእነዚህም ዓመታት መና ከደመና
እየወረደላቸው ውሃ ከደንጊያ እየፈለቀ
ላቸው ሲመገቡ የኖሩት በመልአኩ ቅ/
ሚካኤል እጅ ነበር ይህንንም ቅዱስ ያ
ሬድ "በእደ ሚካኤል ሴሰዮሙ ዓርብአ
ዓመተ በገዳም ለሕዝቡ" በማለት ዘም
ሯል ወደአማርኛ ሲተረጐም ሕዝቡን
በሚካኤል እጅ አርባ ዓመት መገባቸው
ነው ።

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



# የእግዚአብሔር ታቦት

ታቦት ማለት የቃል ማደሪያ ማለት
ነው ። እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ
ሲና ተራራ በክብር ተገልጾ አሠርቱ
ቃላትን በጽላቱ ላይ ጽፎ እንደሰጠው
የታመነ ነው ፤ ይህም የሆነው ከክርስ
ቶስ ልደት በፊት በ፩ሺ፬፻፵፰ ዓመተ
ዓለም ነው፣ ለሙሴም በጽላቱ ላይ ተጽ
ፈው የተሰጡት ሕግጋት የሚከተሉት
ናቸው ።

እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ የእ
ግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከ
ንቱ አትጥራ የሰንበትን ቀን አስብ ት
ቀድሰው ዘንድ አባትህንና እናትህን
እርዳ እድሜህ ይረዝም ዘንድ አትግ
ደል ፣
አታመንዝር
አትስረቅ
የባልንጀራህንም ሀብቱንም ሆነ ንብረ
ቱንም አትመኝ ፤ አስረኛውም ሕግ
ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ው
ደድ የሚል ነው ።

(ዘጸ. ምዕ. ፳.ቁ.3-፲፯) ዘሌ. ምዕ.
፲፱. ቁ. ፲፰ እንመልከት ሙሴም ከእግ
ዚአብሔር ታቦተ ሕጉን ከተቀበለ በኋላ
እስራኤልን በሕገ እግዚአብሔር ለመ
ምራት ኃላፊነትን ተቀበለ መሐሪ ይቅ
ር ባይ እግዚአብሔርም ሕጉንና ሥነ
ሥርዓቱን ለሚጠብቁ ሁሉ ዘወትር
ከመካከላቸው እንደማይለይ ነገራቸው
እስራኤልም ሕጉን ጠብቀው ያለምንም
ችግር ይኖሩ ነበር ። ጠላትም በሚነሣ
ባቸው ጊዜ የእግዚአብሔርን ታቦት
ይዘው ሲዘምቱ ኃይል እየሆናቸው ጠላ
ታቸውን ሁሉ ድል አድርገው ይመ
ለሱ ነበር ።

ለምሳሌ በኢያሱ ዘመን የእግዚአብሐ
ሔርን ታቦት ተሸክመው ሲጓዙ ከላይ
እስከታች የሞላው ባሕረ ዮርዳኖስ
ቆሞላቸው በተአምራት በደረቅ መሬት
ተሻግረዋል ።

ከብዙ ዘመን በኋላ ግን የሊቀ ካህ
ናቱ የኤሊ ልጆች በመጥፎ ሥራቸውና
አድራጐታቸው ኃጢአት ሠሩ እግዚአብ
ሔርንም በደሉ አስቆጡትም ስለዚህም
ነገር አባታቸው ኤሊ ልጆቹን ይህን
አስከፊና አጸያፊ ሥራችሁን እግዚአብ
ሔር ስለማይወድ ተው ቢላቸው ሊሰ
ሙት አልቻሉም እኒህም አፍኒና ፍን
ሐስ ነበሩ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በኃ
ጢአታቸው ምክንያት በረድኤት ስለተ
ለያቸው ፍልስጥኤማውያን በጠላትነት
ተነሡባቸው እስራኤላውያን ከኤሊ
ልጆች ጋር ሆነው በአንድነት ታቦተ
ጽዮንን ይዘው ለጦርነት ወደ ፍልስጥ
ኤም ዘመቱ ጦርነትም ገጠሙ ታላቅ
ግድያም ሆነ ካህናቱም የኤሊ ልጆች
በጦር ተወግተው ወደቁ ታቦተ ጽዮን
ም በፍልስጥኤማውያን እጅ ተማረከች
ሊቀ ካህናቱም ኤሊ ታቦተ ጽዮን ስለ
መዝመቷ አዝኖ ተክዞ እንዴት
እንደሆነች በልቡ ሲአወጣና ሲአወርድ
ሳለ አንድ ሰው መጣ አሉት ሰውየው
ንም ከየት መጣህ አለው ከጦርነት አም
ልጬ የመጣሁ ነኝ አለው ኤሊም ልጆ
ችስ ብነግራቸው ብመከራቸው እንቢ
ብለውኛል ታቦተ ጽዮንስ እንዴት ሆነ
ች ብሎ ቢጠይቀው ፍልስጥኤማውያን
ማርከው ወሰዷት አፍኒንና ፊንሐስም
በጦር ተወግተው ሞቱ አለው ።

ሊቀ ካህናቱ ኤሊም ታቦተ ጽዮንን
ይወዳት ስለነበረ መማረኳን በሰማ ጊዜ
ደንግጦ ከተቀመጠበት ወንበር የኋሊት
ወድቆ ተሰበረ የዘጠና ስምንት ዓመት
ሽማግሌ ስለነበር ወዲያውኑ ሞተ ፍልስ
ጥኤማውያንም ታቦተ ጽዮንንማርከው
ከወሰዷት በኋላ ዳጎን ከተባለው ጣኦታ
ቸው በታች አስቀምጠዋት ሄዱ በማግሥ
ቱ የዳጐን አገልጋዮች እንደተለመደው
መጥተው ለማገልገል ዳጎንን ቢመለከቱ
በግንባሩ ተደፍቶ አገኙት እንሥተው
ም እንደገና ዳጎንን በላይ ታቦተ ጽዮንን
በታች አድርገው አስቀምጠው ሄደ
ዋል ።

ተመልሰውም መጥተው እንደልማ
ዳቸው ቢያዩት እጆቹ ተቆራርጠው
ተበታትነው አገኙት የዳጎን አገልጋዮ
ችም ይህን ነገር ከአዩ በኋላ የማይጠ
ቅም የማይረባ ከንቱ መሆኑን ተረድ
ተው ወደ ቦታው አልተመለሱም (፩ኛ
ሳሙ ምዕ. ፭ ፩-፮ ።)

ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር መቅ
ሰፍት በፍልስጥኤማውያን ላይ መጣባ
ቸው በሥጋቸውም የእባጭ ደዌ ያዛ
ቸው አዝመራቸውንም የአይጥ መንጋ
መጥቶ በላባቸው እነርሱም ርሐብ ችግ
ር መከራ ፣ እየጸናባቸው ስለሄደ ስለዚህ
ነገር እንዴት እናድርግ እስከመቸስ እን
ጨነቃለን በእኛ ላይ የእግዚአብሔር
እጅ መቅሰፍት ጠንክራለች የእስራኤ
ልም አምላክ ታቦት አይቀመጥብን
አሉ ።

ተሰብስበውም ወደ ጌት አገር ይሂድ
ምንአልባት ይህ ችግር ይቀልል ይሆ
ናል ሲሉ ወሰኑ ታቦተ ጽዮንንም ወደ
ጌት አገር ላኳት ይዘዋት ሲሄዱ ከተማ
ው እንደደረሱ በዚያም የእግዚአብሔር
መቅሰፍት ገባባቸው እነሱም ከሞት
የሚአደርስ ድንጋጤ ስለደረሰባቸው
የጌት ሰዎችም እኛንና ሕዝባችንን ሊገ
ድሉ የእግዚአብሔርን ታቦት አመጡ
ብን ብለው በታላቅ ድምፅ ጮሁ በሀገር
ያሉትን አስማተኞችንና ሟርተኞችን
ጠርተው በእግዚአብሔር ታቦት ላይ
ምን እናድርግ እስቲ ንገሩን ከዚህ መከ
ራ እንዴትስ ማምለጥ እንችላለን አሏ
ቸው የእግዚአብሔርንም ታቦት አስወ
ጥተን እንስደድ ቢሏቸው እነርሱም የእ
ግዚአብሔርን ታቦት ወደ ሀገሩ ስትመ
ልሱ ባዶውን አትስደዱት ስለ በደልም
ካሣ መሥዋዕት አቅርቡለት አሏቸው ።

እነዚያም ስለበደል ካሣ የምንመልስ
ለት ምን እለ አሉ እነርሱም አምስት



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በዛሬው ልማት በቤተ ክርስቲያን ዓምዳችን ለአንባብያን የምናቀርበው በወለጋ ሀገረ ስብከት በነቀምቴ ከተማ ስለተጀመረው የልማት እንቅስቃሴ ነው ፤ በከተማው አምስት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ እነርሱም ፡

፩ኛ ቅድስት ማርያም
፪ኛ ገነተ ኢየሱስ
፫ኛ ደብረ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ
፬ኛ ቅዱስ ገብርኤል
፭ኛ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ናቸው ።

ለእነዚህ አምስት አድባራት የሚያገለግል ወፍጮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተሰጥቷቸው ወፍጮው ተተክሎ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

ወፍጮው በተተከለበትም ቤት አካባቢ ለልዩ ልዩ አትክልትና አዝርዕት መትከያና መዝሪያ የሚሆን ሰፋ ያለ ቦታ ሲኖር በጥቂቱ መሬት ላይ ካሮት፣ ሽንኩርት ፣ ጥቅል ጎመን ተተክሎበታል ። በተጨማሪም ፭፻ የጥድ ችግኞች ተተክለው በጠቅላላ የጸደቁ መሆናቸውን በዓይናችን ዓይተን ለመረዳት ችለናል ።

ለወደፊት ስላለው ዕቅድ የሀገረ ስብከቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ጫን ያለው እየነውን ጠይቀናቸው ሲያብራሩ ፣ ወፍጮው የሚፈጨው ጥራጥሬ ብቻ በመሆኑ በጣም ተቸግረናል። ጥራጥሬውን ሲፈጭ ቆይቶ ጤፍ ሲፈጭበት ስለሚሸረከት ብዙ ደንበኞችን ለማግኘት አልቻልንም ይህንን ችግር ለማስወገድ ከቅዱስ ፓትርያርኩ የጤፍ ወፍጮ እንዲሰጠን ጠይቀን ስለተፈቀደልን ያ የተፈቀደው የጤፍ ወፍጮ በተተከለ ጊዜ በአምስቱም አድባራት ለሚያገለግሉ ካህናት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አንጠራጠርም ። ብለዋል። ሊቀ ካህናት ጫንያለው እየነው ማብራሪያቸውን በመቀጠል በወፍጮው ቤት አካባቢ እንድናለማው መንግሥት የፈቀደልን 7.000 (ሰባት ሺህ ካሬ ሜትር) ነው ይህም በስተግርጌው የማይነጥፍ ውሀ ያለው በመሆኑ በጋ እስከ ክረምት ምግብነት ያላቸውን አትክልት ለማብቀልና ለመጠቀም ያስችለናል ከሚቀጥለው ወር ጥቅምት አንድ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ጀምሮ የአምስቱም አድባራት ካህናት በኅብረት የልማቱን ተግባር ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ በማለት የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል።

በዚሁ ከተማ ከሚገኙት አምስት አድባራት አንደኛው ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል መሆኑ ከላይ ተገልጿል በተጠቀሰው ደብር መስከረም ፲፪ ቀን ፹፱ ዓ.ም በመገኘት ለምእመናን ትምህርተ ወንጌል ሰጥተናል ከትምህርታችንም በኋላ በደብሩ አካባቢ የተፈጸሙትንና የሚፈጸሙትን የልማት ተግባሮች በደብሩ አስተዳዳሪ በመልአከ ሣህል ሳሙኤል አስጎብኚነት እየዞርን ተመልክተናል ።

በተመለከትናቸውም የልማት እንቅስቃሴዎች ወ/ሮ ጥሩነሽ ቡሌ የተባሉ የሰበካ ጉባኤ ንብረት ያዥ የተከሏቸውን ፭ሺህ የባሕር ዛፍ ተክሎች ተመልክተናል ። ወ/ሮ ጥሩነሽ ቡሌን ስለተክሎቹ ጠይቀናቸው ሲገልጹ እነዚህን ባሕር ዛፎች የተከልኳቸው እኔው ራሴ ከደን ልማት ሄጄ ችግኞችን ጠይቄ በማምጣት ነው ። እኔ ከግል ገንዘቤ አውጥቼ ሠራተኛን በመቅጠር ራሴም ከልጆቼ ጋር ሆኜ በመሥራት ተክዬ በማጽደቅ ከዚህ አደረስኳቸው እንጂ ከካህናቱም ሆነ ከምእመናኑ እስከ ዛሬ ድረስ የረዳኝ የለም በማለት ገልጸውልናል ። ወ/ሮ ጥሩነሽ በተጨማሪ በግል ገንዘባቸው ብር ፲፪ሺህ አውጥተው ወደር የማይገኝለት እጅግ በጣም ያማረና የተዋበ ዕቃ ቤት አሠርተው ለቤተ ክርስቲያኑ መገልገያ እንዲሆን አበርክተዋል ።

እኚህ በጎ አድራጊ ሴት በየወሩ የሚካኤል ዕለት ሰንበቴ ተቋቁሞ ችግረኞች በምግብና በልብስ እንዲረዱ ሕዝበ ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ ተግባር ከማነቃቃታቸውም ሌላ ለሰንበቴው ማኅበር መሰብሰቢያ የሚሆነውንም አዳራሽ እንዲሠራ ከሁሉ የበለጠ ፬ሺህ ብር ያወጡ መሆናቸውን የደብሩ አስተዳዳሪ ገልጸውልናል ።

በተጨማሪም በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ስም ፈልቆ ልዩ ልዩ ደዌ ይዞ የሚያሰቃያቸውን የሚፈውስ ፀበል መንገዱ አስቸጋሪና ለተጠማቂዎችም የማይመች የነበረውን ከግል ገንዘባቸው አውጥተው መንገዱን በማሠራት በሽተኞች ያለ አንድ ችግር ተጠምቀው እንዲፈወሱ ማድረጋቸውን ተረድተናል፣

ወይዘሮ ጥሩነሽ ቡሌ በጉልበታቸውም ሆነ በገንዘባቸው ለቤተ ክርስቲያናችን የከፈሉትና የሚከፍሉት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ለሌሎች ሴቶች መልካም አርአያነት ያለው የሥራ ፍሬ ስላሳዩ ሊመሰገኑ የሚገባቸው ሴት ናቸው በዚህ ደብር አጥቢያ የሚገኙት እርሳቸው ብቻ አይደለም ሌሎችም ይገኛሉ ነገር ግን በመልካም ሥራቸው ከሁሉም ቀድመው አግኝተናቸዋል ።

ነቢዩ ሆሴስ ማነው ጠቢብ ይህችንስ የሚያስተውል የሚያውቃትም የእግዚአብሔር መንገድ የቀናች ናትና ጻድቃን ይሄዱባታል ተላላፉዎች ግን ይወድቁባታል ብሎ እንደተናገረው የቀናች የእግዚአብሔር መንገድ ማለት በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በጉልበትና በገንዘብ እንደ ወ/ሮ ጥሩነሽ መልካም ሥራ መሥራት ነው ጻድቃን ይሄዱበታል ተላላፊዎች ግን ይወድቁበታል እንደተባለው ጻድቃን መልካም ሥራ ለመሥራት የሚሽቀዳደሙ ሲሆኑ ኃጥአን ግን እንኳን ራሳቸው ሊሠሩ የሚሠራውንም ደግ ሰው እንዳይሠራ ልዩ ልዩ መሰናክል ያስቀምጣሉ ስለዚህ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በፊቱ የሚደቀንበትን ችግር በመታገሥ ሃይማኖቱን ጠንክሮ የመጠበቅ ሥነ ምግባሩንም የማሳመር መንፈሳዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን መዘንጋት የለበትም ።

ለልማት አመች ሆኖ ከተገኘ በየአንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት አጥቢያ እንዲቋቋም በሰበካ ጉባኤ የተመረጡ ካህናትና ምእመናን አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል ሐዋርያው ጳውሎስ "ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘዝናችሁ ነበር ሥራ ከቶ ሣይሠሩ በሰው ነገር እየገቡ ያለ ሥርዓት ስለሚሄዱ ሰምተናል ። እንደ ዚህ ያሉትም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዝዛቸዋለን እንመክራቸውማለን እናንተ ግን ወንድሞቼ ሆይ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ በማለት ለተሰሎንቄ ሰዎች መልእክትን አስተላልፎላቸዋል ። ፪ኛ ተሰሎንቄ ፫፡፰-፲፫ ።

ካህናት በበዓላት ቀን ቀድሰው በሥራ ቀን ሠርተው የራሳቸውን ኑሮ ከማሻሻል ጋር ለምእመናንም ተፈላጊውን አገልግሎት ለማቅረብ የሚችሉት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የልማት ተግባር ከላይ ስማቸው እንደተጠቀሰው በጎ አድራጊት ሴት በጉልበታችንም ሆነ ገንዘባችን የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባትን ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባትን ቤተ ክርስቲያናችን እና ገልግላት ልማት በቤተ ክርስቲያንም ማለት በገንዘብም በጉልበትም በምክርም ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልበትን መልካም መንገድ መቀየስ ነውና ።

ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ

የወርቅ አባሎች አምስትም የወርቅ አይጦች አቅርቡ የአባጬችሁንም ምሳሌ ጭምር አድርጋችሁ ለእስራኤል አምላክ ታቦት ክብርን ስጡ በምድራችሁም ሰላም ታገኛላችሁና ሠረገላም ሥሩ ቀንበር ያልተጫነባቸውን የሚያጠቡትንም ሁለት ላሞች በሠረገላ ጥመዷቸው ስለበደልም ያቀረባችሁትንም በሣጥን አድርጋችሁ የእግዚአብሔርን ታቦት የወርቁንም ምሳሌ ያሉበትን ሣጥን በሠረገላ ው ጭናችሁ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ሀገሩ ስደዱት አሏቸው ሸኙተውም ሰደዱት እስራኤልም በክብር ተቀበሉት ዛሬም ቢሆን በሀገራችን በየክብረ በዓሉ በየንግሡ ታቦተ ሕግ ሲወጣ ምዕመናን ታቦቱን አጅበው በታላቅ ድምቀት በልዕልታ በልዩ ልዩ የምስጋና መዝሙሮች እየዘመሩ የሚታዩት ከዚያ ተያይዞ የመጣ ስለሆነ ነው ። በመሆኑም ሕዳር ፳፩ ቀን በየዓመቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጽላቱ ባለበት ሁሉ በታላቅ ክብር ተከብሮ ይውላል ።

እንግዲህ የዚህ ሁሉ በረከት ተካፋዮች ስለሆንና ከእግዚአብሔርም የተሰጠን ይህ ክብር ለእኛ ለምእመናን በመሆኑ እያንዳንዳችን የእግዚአብሔርን ታቦት በማክበር ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና መስጠት እንዳለብን ተረድተን ዘወትር እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማክበር የተጋንና የነቃን እንሁን ።

መምህር ወልደ አማኑኤል ወ/አገኘሁ

# መልአኩ ቅዱስ ....

ከገጽ ፰ የዞረ

እግዚአብሔር አምላክ ሕዝበ እስራኤልን የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር እንዳይጐዳቸው ሌሊት በእሳት ብርሃን ቀን በዓምደ ደመና ይመራቸው ነበር የሚመራቸውም መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ነበር "እንዘ ሚካኤል የሐውር ቅድመ ትዕይንቶሙ ለእስራኤል ትርጓሜው ሚካኤል በእስራኤል ሠራዊት ፊት ለፊት ሲሄድ በማለት ሊቁ ቅ/ ያሬድ ገልጾታል ።

የፈርዖን ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ በምድር ላይ በሚኖሩ ፍጡራን ላይ ልዩ ልዩ በሽታዎችን እንዳመጣ ተመልክተናል ይህ እንዳይሆን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ይገባናል እግዚአብሔር ምህረቱ የበዛ መዓቱ የራቀ ስለሆነ ፈጥኖ ተቆጥቶ ፍጥረቱን አያጠፋም ታግሦ ታግሦ ግን አጥፊው ከጥፋቱ ተመልሶ ንስሐ ካልገባ ለጥፋት የተዘጋጁትን መላእክት ልኮ እንደፈርዖን ይቀጣቸዋል ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ እግዚአብሔር የኃይሉን መቅሠፍት ለማሳየት በፈለገ ጊዜ ታግሦ ታግሦ ለጥፋት የተዘጋጁትን መላእክት ይልካቸዋል ፤ እንዲሁም ይቅርታውን ለመግለጽ ሲፈልግ ለይቅርታ የተዘጋጁትን መላእክት ይልካል ብሏል ። (ሮሜ ፱፡፳፫)

እግዚአብሔር አምላክ ለወዳጆቹ የሚመራ መልአክ ምሕረት ይልክላቸዋል ለምሳሌ መልአከ መዓቱን ልኮ የሰናክሬምን ሠራዊት እንዲደመስስ ሲያደርግ መልአከ ምሕረቱን ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ሕስቅያስን ከጥፋት አድኖታል (ትን.ኢሳ.፴፯. ፴፮)

እንዲሁም ከላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ወዳጆቹ እስራኤልን በቅዱስ ሚካኤል መሪነት የኤርትራን ባሕርን ከ





www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቲያናዊ ሕይወት

## ከመምህር ሀብተማርያም ተድላ

ክርስቲያናዊ ሕይወት ስንል የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መመሪያ ተከትለው በስሙም ክርስቲያን ተብለው በተጠሩት በቅዱሳን ሐዋርያት ትምህርትና ትእዛዝ ጸንቶ መኖር ማለታችን እንደሆነ ባለፈው ጽሑፋችን በመጠኑ ገልጸናል ።

ይህ መሆኑ ከታወቀም ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ምን ሲል አስተማረ ? ምንስ ሠራ ? ምን ዓይነት ትእዛዝስ አዘዘ? ብሎ መጠየቅና መመራመር አስፈላጊ ይሆናል ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፤

ትምህርት

ሥራና ትእዛዝ

፩ኛ. ትምህርት፡- በተራራ ላይ ሁኖ በሚያስተምርበት ጊዜ ብዙዎች ሰማዕያን፡-"ይህ ሰው ሙሴ የሰጠንን ኦሪትንና አበው ነቢያት የጻፉአቸውን መጻሕፍት ሊሽር የመጣ ነውን? የሚል ሕሊና ያደረባቸው መሆኑን አውቆ፡-" ኦሪትንና ነቢያትን ማለትም በኦሪት የፍሎ ሲያሻግር ግብጻውያን በባሕር ውስጥ ሰጥመው እንዲቀሩ አድርጓል እስራኤላውያንን ከባርነት ቀንበር ነፃ አድርጎ በነፃነት እንዲኖሩ ያደረገ አምላክ ቀድሞ ዓለም ሳይፈጠር ነበር ዛሬም አለ ወደፊትም ለዘለዓለም ይኖራል ።

መሻገሪያው በሩ መውጫው ቀዳዳው መላ ቅጡ ጠፍቷቸው ይጨነቁና ይቸገሩ የነበሩትን ሕዝበ እስራኤልን መልአኩን ልኮ ባሕሩን ከፍሎ በማሻገር ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳነ አምላክ መልአኩን ቅዱስ ሚካኤልን በረድኤት ልኮ ከችግራችንና ከጭንቀታችን ያድነን አሜን ።

ቀ. ልሣነ ወርቅ ፀሃብሳ

ታዘዘውን ፣ በነቢያት የተነገረውን ትንቢት እፈጽም ዘንድ የመጣሁ እንጅ እሽር ዘንድ የመጣሁ አይምሰላችሁ ። እውነት እላችኋለሁ ፣ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከኦሪት ሕግ አንዲት ነጥብ አታልፍም ። ከእነዚህ ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር እንዲሁም የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ያነሰ ይሆናል ።

አሥሩን ትእዛዛት የሚፈጽም ግን በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይሆናል ። ለቀደሙት አባቶቻችሁ አትግደል ፣ ነፍስን የገደለ ይፈረድበታል ፣ ተብሎ ከእናንተ በፊት ለነበሩት ሰዎች ታዞ የነበረውን ትእዛዝ ሰምታችኋል ፤ እኔ ግን እላችኋለሁ ነፍስ መግደል ቀርቶ ወንድሙን ያስቆጣ በገሃነመ እሳት ይፈረድበታል ። ወንድሙን ድሀ ወይ ጨርቅ ለባሽ አባተ ታናሽ ብሎ የሰደበ ይፈረድበታል ። ቀጥሎም መባህን ይዘህ ወደ ቤተእግዚአብሔር በምትሄድበት ጊዜ ወደ ነቀፍከውና ያሳዘንከው ወንድምህ ሂድና ይቅር በለኝ ብለህ ከእግሩ ወድቀህ ታረቅ ። ከዚያ በኋላ መባህን አቅርብ ብሏል ። እንግዲህ፡- ከቤት ከጐረቤት ጋር እየተጣሉ የቂምና የበቀል ጐተራ ሆኖ የሰላምን ዳብዛ አጥፍቶ እግዚአብሔርን እወዳለሁ ብሎ መሥዋዕት ከማቅረብ ይልቅ በመጀመሪያ ሰላምን መመሥረት ፣ ከማንኛውም የተፈጥሮ ወንድም ጋር በፍቅር መኖር አንደበትን ክፉ ከመናገር ሰውን ከማስቀየም መከልከል መቅደም እንዳለበትና አስቀድሞ የተፈጸመ ስሕተት ካለ ቶሎ ብሎ ማረምና በንስሐ መመለስ እንደሚገባ ያስገነዝበናል ።

ከዚህም አያይዞ "አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል ፤ እኔ ግን እላችኋለሁ የዝሙትን ሥራ በግብር መግለጽ ቀርቶ ሴትን አይቶ የተመኛት ሁሉ፡- ያንጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመነዘረ፤ ብሏል ።

ይህም ትምህርት የሚያመለክተው ያሉትን ሁሉ እየተመለከቱ በፍትወት ከመቃጠል ይልቅ የምትሆነውን (የሚሆናትን) መምረጥና ማግባት ከምኞትና ከሕሊና ዝሙት ነፃ ሆኖ መኖር የሚገባ መሆኑን ነው ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ተመልክቶ ነው "ይኄይስ አወስቦ እምዋዕይ በፍትወት" በምኞት ሲቃጥሉ ከመኖር ይልቅ ማግባት ይሻላል ያለው ።

ሐዋርያው ስለዚሁ ጉዳይ በሰፊው ሲያብራራ ይኄይሶ ለብእሲ ኢቀሪበ አንስት ካለ በኋላ፡- ወከመሰ ኢትዘምው ኩሉ ብእሲ ይንበር በብእሲቱ ወኵላ ብእሲት ትንበር በምታ/የዝሙትን ሥራ እንዳትሠሩ፡- ወይም በምኞት እንዳትቃጠሉ ወንድ ሁሉ በሚስቱ ይኑር ማለት ሚስት ያግባ ሴትም ሁሉ ባል ይኑራት ባል ፣ ታግባ በምኞት ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና ፩ኛ ቆሮ ፯፣፲፣

ሚስትን መፍታት ስለአለመገባቱ፡-

"ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የተፈታችበትን ምክንያት ገልጾ ይጻፍላት ከዚያም ይፍታት ያሰናብታት ተብሎ ከእናንተ በፊት ለነበሩት አባቶች መታዘዙን ሰምታችኋል ። እኔግን እላችኋለሁ ፤ በላዩ ላይ የዝሙት ሥራ ሳትሠራ የዝሙት ወንጀል ሳትፈጽም ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እሱ ራሱ ዘማ(አመንዝራ) አደረጋት" በዝሙት ተገኝታ የተፈታችውን ያገባም በደለ ፤ ኃጢአት ሠራ ። ብሏል ፣ በሌላም ጊዜ ፈሪሳውያን ሊፈትኑት መጡና፡- በማንኛውም ዓይነት በደል ብትበድለው ወንድ ሚስቱን ሊፈታ ይገባዋልን ሲሉ ጠየቁት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመሠረቱ እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው በኦሪት የተጻፈውን አላነበባችሁምን ስለዚህም ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል ፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ፤ እንኪያስ አንድ እንጂ ሁለት አይደለም ። እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለይ አይገባውም ። ብሎአቸዋል ።

ማቴ፲፱

ይህ ትምህርት በክርስትና ዓለም ውስጥ ክርስቲያናዊ ሕይወት ላላቸው ሁሉ አንደኛውና ከፍተኛው መመሪያቸው ነው ። ሁለቱም ተቃራኒ ጾታዎች ተዋድደውና ተማምነው ሕይወታቸውን በአንድነት አዋኽደው "ከሞት በቀር የሚለየን የለም ብለው የእግዚአብሔርን ስም ጠርተው ከተጋቡ በኋላ፡- ከዝሙት በቀር የሚለያቸው ሌላ ኃይል አለመኖሩን ያስገነዝባል ማንኛውም ስሕተት በንስሐ ሊወገድ ይችላል ፤ ንስሐሰ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመ ዘኢአበሰ፡ ወለዘማኒ ትሬስዮ ከመድንግል (ንስሐ በደለኛውን እንዳልበደለ ፤ ሴሰኛውን እንደ ድንግል ታደርገዋለች) ተብሏልና ።

ስለዚህ በክርስትና ዓለም ፍች የተከለከለና የተነወረ መሆኑን ያስገነዝባል።

ሥራ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ምን ሠራ ? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዐረገበት ድረስ የሠራቸው ሥራዎች እንደሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ እጅግ የበዙ ናቸው ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለዚህ ጉዳይ ሲያብራራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራቸው ሥራዎች ሁሉ ቢጻፉ መጻሕፍቱን ዓለም በሙሉ ሊሸከማቸው ባልቻለ ነበር። ነገር ግን እናንተ እንድታምኑና አምናችሁም የዘለዓለምን ሕይወት እንድትወርሱ ይህን ጻፍንላችሁ ይላል ዮሐ ፳ እና ፳፩ በጥቂቱ ለመመልከት ያህል ክርስቶስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ እስከ ተጠመቀበት ጊዜ ድረስ ቤተ ሰዎቹን እያገለገለ ነበር ያደገው ። ያስተምርበት ከነበረው ተራራ በወረደ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተከተሉት ። አንድ በለምጽ ደዌ የተያዘ ሰው መጣና ሰገደለት ፤ ፈቃድህ ከሆነ ልታነጻኝ ትችላለህ" በማለት ካደረበት ደዌ እንዲፈውሰው ለመነው ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፈቅጃለሁ አለውና ዳነ ። ከዚያም የተለያየ ዓይነት በሽታ የሚያሰቃያቸው ብዙ ሰዎችን ፈወሰ ፤ ማለትም ለምጻሞችን አነጻ፣ እውራንን አበራ ፤ አንካሶችን አዳነ ፤ ሙታንን አስነሣ ፤ ርኁባንን አጠገበ ። በሥራው ሁሉ የተደነቀና የተመሰገነ ሆነ ። ደቀ መዛሙርቱም ይህን የመምህራቸውን ሥራ በመከተል ድውያንን እንደፈወሱና ሙታንን እንዳስነሱ በየመልእክታቸውና በየገድላቸው ተመዝግቦላቸዋል ።

ራሱ ወደ ዓለም ዙሪያ ሒዱና አስተምሩ ብሎ በላካቸው ጊዜ "ሕሙማንን ፈውሱ ፤ አጋንንትን አስወጡ ፣ ለምጻሞችን አንጹ ሙታንን አስነሡ" ብሎ ሥልጣን ሰጥቷቸው ነበር። ያ የሰጣቸው ሥልጣን በእነሱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በምግባር ለሚከተሉአቸው ክርስቲያኖች የተሰጠ ስለነበር የሐዋርያት ተከታዮች ካህናትና ቅዱሳን ሠርተውበታል ። አሁንም ፍጹም ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚኖር ክርስቲያን ሊጠቀምበት የሚችል ነው ። ነገር ግን የሃይማኖትና የምግባር ሕፀፅ ካለ ምንም ማድረግ አይቻልም ማቴ ፲፯፣ ፲፱-፳፩ ፣

ትእዛዝ "ጠላትህን ጥላ ፤ ወዳጅህን ውደድ" የተባለውን ሰምታችኋል ፤ እኔ ግን እላችኋለሁ ጠላታችሁን ውደዱ ፤ ለሚያሳድዱአችሁም መርቁአቸው ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉላቸው የሚእፈቅሩአችሁንም ብታፈቅሩ ምን ዋጋ አላችሁ ይህንማ ግብዞች ሁሉ ያደርጉት የለምን? ሰማያዊ አባታችሁ ፍጹም ነውና እናንተም ፍጹማን ሁኑ ካለ በኋላ ምጽዋት ስትሰጡ ለዓይነ ሰብእ ፣ ለውዳሴ ከንቱ ፣ ለታይታ አታድርጉት ፤ ይህንማ ካደረጋችሁ ዋጋ የላችሁም ምጽዋት በምትመጸውትበት ጊዜ ቀኝ እጅህ እንኳ የምታደርገውን ግራ እጅህ አይወቅ (ለዚህ በጎ ምግባር ቤተ ሰዎችህ ስንኳ ምክንያት ሊሆንብህ አይገባም) በምትጸልዩበትም ጊዜ እንደ ሰነፎች አትሁኑ ፤ ግብዞች በየአደባባይ መቆምና መጸለይ ይወዳሉ ይህንም ሰው እንዲያይላቸውና አቦ አቦ እንዲባሉ ያደረጉት ስለሆነ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን አጡ ። እናንተ ግን ስትጸልዩ ከቤታችሁ ግቡ፤ መስኮታችሁን (መዝጊያችሁን) ዝጉና በሥውር ወደሚያያችሁ አባታችሁ ጸልዩ፤ ስትጸልዩም በአጭሩ በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ ፤ በደላችንንም ይቅር በለን ፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንል ዘንድ ፤ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ፤ ከክፉ አድነን እንጂ ፤ ኃይልም ሥልጣንም ያንተ ናትና ለዘለዓለሙ ብላችሁ ጸልዩ ሲል አዘዘ ትእዛዙን መከተል ክርስቲያንነት ነው ።





www.ethiopianorthodox.org

# ከብፁዓን አባቶች አቡነ ያዕቆብ ሊቀ ጳጳስ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት መካከል አንዱ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ናቸው ። በዚህ ጽሑፍ ለማቅረብ የፈለግነውም ስለ ሕይወት ታሪካቸው በአጭሩ ነው ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የመጀመሪያ ስማቸው ዘፈረ ብርሃን ነው ብፁዕነታቸው በ፲፰፻፺፰ ዓ/ም ሰላሌ አውራጃ እንሣሮ ወረዳ ስላሽ ኪዳነ ምህረት ከአባታቸው ባሻ ገብረ ጻድቅ ሀብተማርያም ከእናታቸው ወ/ሮ በየነች ወንድም ተገኝ ተወለዱ ዕድሚያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከመምህር ገብረ ሕይወት ፊደል ቆጥረው ዳዊት ከደገሙ በኋል ወደሽንኩርት ቅዱስ ሚካኤል በመሄድ ከአለቃ ብርሃኑ ፀዋትወ ዜማ ተምረዋል፤ በተጨማሪም ወደ ዜና ማርቆስ ሄደው ከመሪጌታ አጽመ ጊዮርጊስ ቀደም ሲል ተምረውት የነበረውን ዜማ ከከለሱ በኋላ ድጓና የጾም ምዕራፍ በሚገባ ተምረዋል ወደ ጐንደርም ክፍለ ሀገር ሄደው ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ ማኅደረ ማርያም ከምትባለው ስመ ጥር ደብር ከመሪጌታ ወርቁ ያኑ የተማሩትን ለማጠናከር ችለዋል ።

ከዚያም ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር ሄደው ላስታ አውራጃ ቡግና ወረዳ ብርኳኳ ማርያም ከመምህር ጽጌ ቅኔ ከእነ አገባቡ ተምረው ለማስተማር ከሚያበቃ ደረጃ ደርሰዋል ፤ በተጨማሪም መምህር መንበሩ ወደተባሉት መምህር ሒደው የቅኔን አገባብ ከእርባ ቅምሩ ጋር ከተማሩ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ወደብርኳኳ ማርያም ተመልሰው የተማሩትን የቅኔ ትምህርት እያስተማሩ የሐዲስን ትርጓሜ ከመምህር ኪዳነ ማርያም ተምረዋል ።

የሐዲስን ትርጓሜ ተምረው ከጨረሱ በኋላ ወደትግራይ ሀ/ስብከት በመሄድ እንደርታ አውራጃ ማየ ወይን ቅዱስ ሚካኤል ከተባለው ደብር አምስት ዓመታት ቅኔ በማስተማር ብዙ ካህናትን አሠልጥነው ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።



ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ

ከትግራይ ሀ/ስብከት እንደገና ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር በመሄድ ዓምደ ወርቅ ቂርቆስ ከተባለው ደብር ከአለቃ ካሣ ተክሌ አቋቋምን ከመሪጌታ በለጠ የጐንደር አቋቋምን ተምረዋል ።

ቅዳሜ ቅዳሜ የእሁድ መዝሙርን ዓመት በዓል ከመድረሱ በፊት የዓመት በዓሉን ቀሰም ለተማሪዎቻቸው ስለሚያሰጡኑ የተማሮቹ ቁጥር በርከት ያለ ነበር ። በዚያም በርከት ያሉ ሊቃውንትን አስተምረው ለመምህርነት አብቅተዋል ። በዚያ 6 ዓመት እያስተማሩ ከቆዩ በኋላ ተማሮቻቸውን አስከትለው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ቅኔ ማስተማራቸውን ቀጥለዋል ።

በዚሁ ደብር እያስተማሩ ለጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ወደ አዲስ ዓለም በመሄድ ፯ ዓመት ቅኔ አስተምረዋል ከዚያም እልቅና ተሹመው ወደ መናገሻ ማርያም ሄደዋል ። ቀጥሎም አሰላ ደንጊያ ማርቆስን ተሹመው አስተዳድረዋል ። ከዚያም የደብረ ሊባኖስን ገዳም ተሹመው አስተዳድረዋል ። እንዲሁም የፍርኩታ ማርያም መምህር ሆነው ሲያስተዳድሩ ለጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ የዝቋላ ገዳም አበምኔት ሆነው በመሾም ገዳሙን አስተዳድረዋል ።

በዚያ እንዳሉ ለሢመተ ጵጵስና ወደግብፅ ተልከው የኤጲስ ቆጶስነትን ሥልጣን ተቀብለው ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ በመመለስ የወለጋ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሁነዋል ። ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ከ1941-1969 ለ28 ዓመታት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባል በመሆን በመንፈሳዊ አመራር በወለጋ ሀ/ስብከት የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናትን ሲያስተዳድሩ ምእመናንን በሃይማኖት ሲመሩ ኑረዋል ።

ብፁዕነታቸው በመዋዕለ ሢመታቸው የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን አሳድሰዋል ። መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶች እንዲቋቋሙ አረማውያን እንዲጠመቁ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ አገልግሎትን ፈጽመዋል ። በዚህም መልካም ሥራቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ያለ ደስታ ይሠማታል ።

ብፁዕነታቸው ከተቀኟቸው ቅኔዎች ለማስታወስ ቀጥለው ያሉትን አቅርበናቸዋል ።



## የታኅሣሥ ገብርኤል

### የተቀኙት ሥላሴ

ነደ ሰዶም እስራኤላዊ እንዘ ምድረ ሰዶም ይበልዕ ባቢሎናዊት ነድ ርእየ ሕዋሳተ ደቂቅ ሰለሥተ ፤
ተኃብአት እምነጽሮ እሉ ወገብአት ድኅረተ
በጊዜ ሙብልዕ ሰብአ ነጽሮ እስመ ኢይደሉ ምንተ ወበውስተ ግብ ታሕቴተ ነበልባለ እሳት ወረዶት ጸዊራ ቀሱተ እስመ በዝ ትቀድሀ ማያተ ።

### ትርጓሜው ፤

የእስራኤል ወገን ፤ እሳት የሰዶምን ምድር ሲበላ የባቢሎን ነድ የሰለሥቱ ደቂቅን ሰውነት አይታ እነርሱን ከማየት ተሠወረች ወደኋላም ተመለከተች በምግብ ጊኬ ሰውን ማየት አይገባምና የእሳት ነበልባል ሴትም እንስራዋን ተሸክማ ወደ ጉድጓድ ሄደች በዚያ ውሀን ትቀዳለችና ነው ።

## ዘይዕዜ ቅኔ የልደት

### የተቀኙት

አበሳነ ኅድግ ወኄጋየነ እምጣነ ልዑል ወረደ እምነ ልዑል መንበሩ፤ ስላመ ይግበር ማዕከሌነ ወዳግመ በበነገዶሙ ሰላመ ይግበሩ ።
አናብስተ ገዳም ወሐቅል ምስለ እልህምት ተማከሩ
አናቅጸ ጸርነ ሲኦል እምጣነ ተሠብሩ በሥጋዌሁ ለወልድ ወበመስቀሉ ተኃፍሩ አናቅጸ ጸርነ ሲኦል እምጣነ ተሠብሩ

### ወደ አማርኛ ሲተረጐም ፤

እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ በደላችንና ኃጢአታችን ተውልን ደምስስልን በመካከላችን ሰላምን ያደርግ ዘንድ ወልደ እግዚአብሔር ከሰማያዊ ዙፋኑ ወደምድር ወርዷልና ።

ዳግመኛም በየወገናቸው ሰላምን ያደርጉ ዘንድ የዱር አንበሶች ከላሞች ጋር ተማከሩ የጠላታችን ሲኦል በሮች በወልዶ እግዚአብሔር ሰው መሆን ተሠብረዋልና በመስቀሉም አፍረዋልና

### ኩልክሙ ቅኔ ፤

በተኮሮተ እድ ወበትር እለ ትጸርሑ የአክለክሙ እንከ ዘሐለፈ መዋዕል ወጸናጽለ ወርቅ ሀድግ ነሶሳወ ታሕተ ወላዕል
እስመ መንፈሰ ጾም ወቀኖና በእንቲአክሙ አውስኦተ ይክል
ወዋዕየ ትሀርምት እመ ጸንአ ክርሠ ባሕታዊ አጽለለ ታሕተ ጽላሎታ ለዕፀ ኮል

### ለዓለም ፤

እምኅቤነሰ ድኅረ ተኃጥአ ጣዕመ ሐሊበ ላህም እኅል
ኖሎተ እንስሳ ረከብዎ ለሐሊበ እጎልት አማኑኤል
እንዘ በታሕተ እም ኅቡዕ ወበዕፀ ሰግላ ሰቁል
ወማኅሌተ ዚአነ እመ ደክመ ተመርጕዘ በትረ ኃይል
ወልኅበተ አውድነ ይርዓይ እንዘ የዓይል ፤ ማኅሌተ ዚአነ እመ ደክመ ተመርጕዘ በትረ ኃይል ።

### ትርጓሜው

በእጅና በበትር መመታት የምትጮሁ ከበሮና ነጋሪት ሆይ እንግዲህ ያለፈው ዘመን ይበቃችኋል ። የወርቅ ጸናጽልም ወደላይና ወደታች መመላለስሕን ተው ፤ የቀኖናና የጾም መንፈስ ስለእናንተ መልስ ለመስጠት ይችላልና ከምግብ መከልከል ቃጠሎ (ሙቀት) ቢጸና የባሕታዊ ሆድ ከእንኮይ እንጨት ሥር ተጠጋ ።

### ለዓለሙ ፤

ከእኛ ዘንድ የላም ወተት ጣዕም (የላም ልጅ ወተት) ቢታጣ ከብት ጠባቂዎች የጊደሮች ወተት አማኑኤልን ከእንጨት በታች ተሠውሮ አገኙት የእኛ ማኅሌትም በደከመ ጊዜ ኃይል የሚሰጥ በትርን ተመረኰዘ እየዞረ ድካማችን ያይ ዘንድ በትርን ተመረኰዘ ማለት ነው ።

ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ አሁንም በሕይወተ ሥጋ ይገኛሉ ዕድሚያቸው ፺፩ ነው ነቀምቴ ከተማ በመንበረ ጵጵስናው ከሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በዓታቸውን አድርገው በጾም በጸሎት በስግደት ተወስነው ይኖራሉ ።

በሠርክ ከሚደርሰው የማኅበር ጸሎት አይለዩም አንዳንድ አዛውንት ወደ እርሳቸው እየመጡ ምክር ሲጠይቁ ቡራኬም ሲቀበሉ ተመልክተናል በሃይማኖት ጸንቶ ሥነ ምግባርን አሳምሮ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ከእንዲህ ያለ ዕርግና መድረስ በጣም ያስደስታል ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ፩ኛ ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው በማስተማር ፪ኛ መምህርነት ተሹመው ፤ በማስተዳደር ፫ኛ ሊቀ ጵጵስና ተሹመው ሥልጣነ ክህነትን በመስጠት በመባረክ መንፈሳዊ መመሪያም በመስጠት ለሀገራቸው ያበረከቱት መንፈሳዊ አገልግሎት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው ።

ብፁዕነታቸውን ወደፊት ስላላቸው ዓላማ ጠይቀናቸው ሲገልጹ ሕይወቴ በምድር እስካለ ድረስ ስለሀገሬ ስለቤተ ክርስቲያኔ ከመጸለይ አልቦዝንም ብለውናል ሁላችንም ስለሀገራችንና ስለቤተክርስቲያናችን ያለን ፍቅር እንደ ብፁዕነታቸው እስከ ዕድሜያችን ፍጻሜ ሊሆን ይገባል ። ይህም አርአያነታቸውን እንድንከተል ያስገነዝበናል ።

የዜናው አቅራቢ
ቀሲስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# ስብከተ ወንጌል

ክፍል ፭

መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ጸሐፎችና ፈሪሳውያን እንዲሁም ብዙ አማኞች በተሰበሰቡበት በታላቁ በአይሁድ ቤተ መቅደስ ቆሞ ወንጌል ካልተሰበከ ዓለም ሰላምና የህሊና ዕረፍት እንደማያገኝ ስለሚያውቅ የሚከተለውን አስተማረ ። ከተሰበሰቡትም ሰዎች መካከል አንደኛው የነቢዩን የኢሳያስን መጽሐፍ ሰጠው መጽሐፉም የሚለው “የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን ለእውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣና እሰብክም ዘንድ ልኮኛል ” ይህንንም አስተምሮ ከጨረሰ በኋላ መጽሐፉን ለአገልጋዩ ሰጥቶ ተቀመጠ በቤተ መቅደስ የነበሩት ሁሉ ትኩር ብለው ተመለከቱት ክርስቶስም ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ አላቸው ይህም ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ እርሱ የተናገረው ትንቢት ነበር ። የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፬ ቁ. ፲፮-፳፩ ።

ይህ ጥቅስ ጌታችን የሥራው አላማ ይሆን ዘንድ የመረጠው ጥቅስ ነው እነዚህ ቃላት በፍቅር በአገልግሎትም በመንፈስ ቅዱስ መቀባትም በእርሱ በሙሉ ተፈጽመዋል ሰዎችን ተስፋ ከመቁረጥ ከስቃይ ከኃጢአትና ከችግር ከታሰሩበትም ከመንፈስ እስራት ሁሉ ነፃ ያወጣቸዋል የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑትም ሁሉ መንፈሳዊ ነፃነትን ከክብር ጋር ያድላቸዋል ። በመሆኑም ወንጌልንለድሆች እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀባኝ ሲል ክርስቶስ በሕዝቡ መካከል ቆሞ እንዳስተማረ ከምንባቡ ተረድተናል ወንጌል ለድሆች ተሰበከ ሲል አቅጣጫው ወደ ምን ይመራል ? ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ሰላምና የህሊና እረፍት አጥቶ ለተቸገረው ዓለም ወንጌልን አስተምሮ የልብ ሰላምና የህሊና ዕረፍት ለመስጠት ሲሆን ለተራበው ዓለም ደግሞ የህይወት እንጀራ ሊሆንና ድሆችም ሰርተው የሕይወት እንጀራ የሚያገኙበትን መንገድ በወንጌል አማካኝነት ለማስጠት ነው ፣ በሌላ በኩል ወንጌልን ለድሆች ሰበከ ስንል መጀመሪያ እኩልነትን እራስን በራስ ለመግዛት ፣ የሥራ ክቡርነትን አውቆ ሌላው በሠራው መከበር ሳይሆን በራስ ወዝ ሠርቶ እራስን ማክበርና ለሀገርም ለወገንም ለቤተክርስቲያንም ሠርቶ ማትረፍን ይጠይቃል ይህ ከሆነ የምንሠራው ሥራ ሁሉ ለሌሎች ታላቅ የምስራች ይሆናል ።

ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር አምላክ ለአማኞች ሁሉ ሰማያዊ አባት ሲሆን ሰዎች ሁሉ ምንም እንኳን በዘርና በቀለም እንዲሁም በብሔር ቢለያዩም በተፈጥሮ ስለሚመሳሰሉ ወንድማማቾች ናቸው የሞትንም ጽዋ እኩል ይከፋፈላሉ በሞትም ፊት አንዱ ከአንዱ አይበልጥም በዚህ መሠረት ለድሆች ወንጌልን መስበክ የሚለው ቃል በመጀመሪያ ጥሩ ምሳሌ እየሆኑ የወንጌልን ቃል በሥራ ገልጦ ማሳየት ያስፈልጋል ይኸውም ለመርዳት ድሆችን ለማገልገል ከሁሉ አስቀድሞ ድሆችን መውደድና በእኩልነት መመልከት ያሻል ። ከላይ እንዳልነው ሰዎች በተፈጥሮ እኩል ቢሆኑም በጠባቸውና በሁኔታቸው ይለያያሉ እነዚህንም ልዩነቶች በትምህርት ማስወገድ እንጂ እንደ ክቡር እቃ ልንይዛቸው አይገባም ምክንያቱም ሰዎች በዚሁ ዓለም ሲኖሩ አንዱ ከአንዱ በኑሮ ቢበላለጡም በሞት ግን ስለማይለያዩ እኩልነት አላቸው ማለት ነው ፣

ለምሳሌ ፡- የሰውን ህይወት ወይም ኑሮ በዓሣ ልንመስለው እንችላለን ዓሣ በባህር ውስጥ እስካለና በመረብ እስከተያዘ ድረስ የመኖር ነፃነት አለው በመረብ ተይዞ ከባህር ከወጣ በኋላ ግን የመኖር ነፃነትና ህይወት የለውም ። ባህር የዚህ ዓለም ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን የመኖር ነፃነትና ህይወት የለውም ። ባህር የዚህ ዓለም ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን ሰውም በዚህ ዓለም ተወልዶ እስከ ሞተ ድረስ የመሥራትና የመኖር ነፃነት ሠርቶ ያገኘውን የመስጠትና የመንሳት የወንጌል ትምህርት የመስጠት መብት አለው ። መብትና ነፃነትም ማለት ለራሱ ሊደረግለት የሚፈልገውን እሱም ለሌላው ማድረግና ሁሉንም በእኩልነት መመልከት ማለት ነው ይኸውም ረሐብ ፣ ችግር ፣ መታረዝ ወገንን ዘርን እንደማይለዩ ሁሉ ማንኛውም አማኝ ስጦታ ፣ አገልግሎት ፣ ዕርዳታ በሚያደርግበት ጊዜ ከማንም ለማንም ሳያደላ ለሁሉም በእኩልነት ሊሰጥ ይገባዋል ። በዚህ ዓለም የመኖር ትርጓሜው ይህ ነውና ። ይህንንም ካደረግን ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ተልኬአለሁ ሲል ያስተማረውን የክርስቶስን ቃል በሥራችን ደገፍነው ማለት ነው።

ይህንንም ለመረዳት ብንፈልግ መጥምቁ ዮሐንስ የሚገባ የንስሐ ፍሬ አድርጉ እያለ በሚያስተምርበት ጊዜ ሕዝቡ ምን እናድርግ እያሉ ጠየቁት መልሱም ሁለት ልብስ ያለው አንዱን ለሌለው ያካፍል ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ አለ ፤ ሊጠመቁ የመጡት ቀራጮች ደግሞ መምህር ሆይ እኛም በበኩላችን ምን እናድርግ ሲሉ ጠየቁት ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው ሰላም አስከባሪዎች የነበሩትም ጭፍሮች እኛ ደግሞ በበኩላችን ምን እናድርግ ሲሉ ጠየቁት እርሱም በማንም ግፍ አትስሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ ፣ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ አላቸው ሉቃስ ም.፫.ቁ.፲-፲፬ ዮሐንስ እውነተኛ ካህን እንደመሆኑ መጠን ሁሉም ተደጋግፎ መኖር እንደሚገባውና አንዱ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌላውም የሚኖር መሆኑን አስተምሯል ።

በተጨማሪም ማንኛውም ሠራተኛ ደመወዙ ብቻ እንዲበቃው በገዛ ላቡ እንዲጠቀም እንጂ በሌላው ላብ እንዳይከበር በሚገባ ሠርቶ የሚገባ የንስሐ ፍሬ እንዲያፈራ ሰብኳል ። ስለዚህ ወንጌል እኩልነትን ማህበራዊ ኑሮን የሚያበስር ታላቅ የምሥራች ነው ፤ ሊባል የሚገባው በዚሁ መንገድ ነው ።

አርስቶትል የተባለው ፈላስፋም ቀደም ብሎ ሲናገር “አገር የጋራ ነው ሰውም በማህበር የሚኖር ፍጡር ነው በሆነ አጋጣሚ በጠባይ ምክንያት አገር የሌለው ሰው ቢኖር እሱ ከሰብአዊ ተፈጥሮ አኗኗር የተለየ ህይወት አለው ማለት እንችልም ይህ ሰው ከጎሳና ከወገን ጋር ባለመግባባት ህግና ሥርዓት ሃይማትና ምግባር ሳይኖረው ቀርቶ እንጂ አገር አጥቶ አይደለም ” ብሏል ።

ሆሚር የተባለው ፈላስፋም በበኩሉ ከማንኛውም ነገር ፍሉጥ የሆነ ጠብ ጫሪና በጥባጭ ይሆናል ፣ ይህ ሰው ብቻውን እንደሚበር አሞራ ነው ” ብሏል ። እርግጥም ሐኪም ሆኖ የታመሙትን ወገኖቹን የማያክም ፡- አዋቂም ሆኖ በድንቁርና ጨለማ ውስጥ ያሉትን ወገኖቹን የማያስተምር ከማህበራዊ ኑሮ የተለየ አውሬ እንጂ ሰው አይባልም ። ሀብት እያለው የተራቡትን የተቸገሩትን ወገኖቹን የማይረዳና ፡- ሁለት ልብስ እያለው አንዱን ልብስ ለተራቆተ የማይሰጥ ብቻውን እንደሚበር አሞራ እንጂ እንደርግብ የዋህ አይደለም ምክንያቱም የመጥፎ ሥራ ውጤቱ ዋጋ ቢስ ሲሆን የመልካም ሥራ ሽልማት ደግሞ በመጨረሻ መንግሥተ ሰማያት የሚያወርስ ነውና ።

ታዋቂው ደራሲ ቶማስም “ዓለም አገሬ ናት የሰው ዘር ሁሉ ወንድሜ ነው። በጎ ሥራም ሃይማኖቴ ነው ” ብሏል ። ይህ ድንቅ አባባል የሚያስረዳን የዓለም ሕዝብ ወሰንና ክልል ሳያግደው ረሐብንና ችግርን ለማስወገድ በአንድነት ተሰልፎ አስጊ የሆነው ጦርነት በዓለም ላይ እንዳይስፋፋ ሰላም እንዲነግስ ሁሉም ሕብረትንና ስምምነትን ይዞ ቢኖር በሀገር ላይ እድገትና ልማት እንደሚገኝ ይገልጻል ። ይህ ሁሉ የሚገኘው በመግባባትና በመተሳሰብ ነው ። መግባባት ካለ ለሌላው ማሰብ ፣ ሌላውን ማገልገል ከሌላው ጋር በእኩልነት መኖር ደስ ይላል መግባባትም ፡- መተጋገዝም መረዳዳት ስለሆነ የድሖውን ችግር ማቃለል ያስፈልጋል ።

ስለወንጌል አላፍርም ያለው ሐዋርያው ጳውሎስም ለሮሜ ክርስቲያኖች በጻፈው መልክቱ በምዕራፍ ፲፪ ቁጥር ፲፰ ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ” ብሏል ይህንንም ያለበት ዋናው ምክንያት ሰዎች በመተሳሰብ ድህነትን ከላያቸው ላይ እንደሚያስወግዱ ለማስገንዘብ ነው እንዳለውም ማንኛውም ህብረተሰብ ከሁሉም ጋር ተስማምቶ በሰላም መኖር ያስፈልገዋል ። በሰላም መኖርም ማለት አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት አብሮ መሥራት ሳይጣሉ ተስማምቶ መኖር ነው ይህን ከሠራን ሰላም አለን ይሁን እንጂ ሌላው እየተራበ እኛ ብንጠግብ ፣ ጎረቤቶቻችን እያዘኑ (እያለቀሱ) እኛ ብንደሰት በአካባቢያችን ያሉት ወንድሞቻችን እራቁታቸውን እየሄዱ እኛ እያማረጥን የምንለብስ ከሆነ ፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ተልኬአለሁ ፤ ያለውን የክርስቶስ ቃል በሥራ ላይ ስላላዋሉ ነው በእኛ ዘንድ ሰላም የለም እውነተኛ ሰላም ግን መረዳዳት ስለሆነ ሌላውን ስንረዳ ሰላም ይኖረናል ፣ ተረጂውም ሰላም ያገኛል ፣ በሰላም የሚሠራ ሥራ ሁሉ መልካም ፍሬን ያፈራልና።

መልካም ፍሬ ማለትም የችግረኞች የደስታቸውና የመከራቸው ተሳታፊ ሆኖ መገኘት ነው እኛም ተካፋይነታችንን የምናስመሰክረው ይህን ሁሉ በነፃ ስንሰራ ነው ፤ ነፃ የምንሆነው ደግሞ እኛ እየሠራን ሌሎችም ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ስናደርግ ነው ፤ ለተጠቁት ነፃነትን መስጠት ፡- ለድሆች ወንጌልን መስበክ የምሥራችም መናገር ማለት ትርጉሙ ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

ይቀጥላል

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፭ የዞረ

ጠቅለል ባለ ሁኔታ አሳጥረን እንደዚሁም ያጠረውን ረዘም አድርገንና ቃላቱን አቀናብረን እናቀርበዋለን ባጭሩ መልሱ ይኸው ነው ።

፬ኛ/ በአንቀጸ ንሥሐ ያለውን ጠቅሰሐል አንድ ሰው ኃጢአቱ ይብዛ ይነስ ለመምህረ ንሥሐው መንገር ግዴታው ነው መምህረ ንሥሰውም የሚሰጠውን ትእዛዝ ይብዛም ይነስም ንሥሐውን ተቀብሎ መፈጸም ነው ።

በንሥሐ የማይደመሰስ ኃጢአት ይኖራልን ስለ ምትለው ግን በንሥሐ የማይሠረይ ኃጢአት የለም ።

፭ኛ/ ለእመቤታችን ፣ ለታቦት፣በቤተ ክርስቲያን መሳለምና መስገድ ለስዕል መስገድም ጣዖትን ማምለክ ነው የሚሉ አሉ ስለ ምትለውም አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ለታቦት ለመስቀል ለጻድቃንና ለሰማዕታት መስገድ ጣዖትን ማምለክ አይደለም ለእነዚህ ከላይ ለተጠቀሱት የጸጋ ስግደት መስገድ አምልኮ ባዕድ አይደለም አምልኮ ባዕድም እንዳይደለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ ሰው ለሰው በጸጋ እንደሚሰግድ ቆርኔሌዎስ ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ሰገደ እንዲህ ይላል ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታ





www.ethiopianorthodox.org

ች ወደቀና ሰገደለት ይላል የሐ.ሥራ ፲፡፳፭ ታዲያ መምላኬ ጣዖት ተባለ ወይ? እንዲህ ከሆነ ቆርኔሌዎስ ለቅዱስ ጴጥሮስ ከሰገደ አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምማ እንዴት የጸጋ ስግደት አይገባትም ይባላል ለእመቤታችን የጸጋ ስግደት አይገባትም ለሚሉስ ቀደም ሲል ክቡር ዳዊት እንዲህ ብሏል (ኩሉ ሙ እለ ይጸልእዋ ለጽዮን ወይኩኑ ከመ ሣዕረ አንሕስት ዘይየብስ ዘእንበለ ይምሐውዎ)እንዲህም ማለት "ጽዮ ንን የሚጠሉ ሁሉ ሳይነቀሉት ወይም ሳያጭዱት እንደሚደርቅ እንደ አሸክት ሣር ይሁኑ ሲል ትንቢት ተናግሮባቸ ዋል ። መዝ

ስለ እመቤታችን ክብር ያልተነገረ ቃል የለም እንዲያውም አንድ ደራሲ ደግሞ ለእመቤታችን የጸጋ ስግደት እንደሚገባት ሲገልጽ ስንኳንስ ለራስዋ ለሥዕልዋ መስገድ እንደሚገባ ዘኢስገ ደ ለስዕልኪ አሥሪያ ምግኤ በሥጋሁ ወበነፍሱ ኢይርከብ ትንሣኤ" ብሏል ለእመቤታችን የጸጋ ስግደት መስገድ ተገቢ መሆኑን በሰፊው መጻፍ ይቻል ነበር ግን የተጠቀሰው ይበቃል "ለጠ ቢብሰ አሐቲ ቃል ትበቁዖ" ይላልና ።

ለታቦትም መስገድ ተገቢ ነው ይኸ ውም "ኢያሱም ልብሱን ቀደደ እርሱና የእሥራኤል ሽማግሌዎችም በእግዚአ ብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግንባራቸው ተደፉ በራሳቸውም ላይ ትቢያን ነሰነሱ" ይላል መጽ ኢያሱ ፯ ፡ ፮ በቤተ ክርስቲያንም መስገድ ተገቢ ነው ሰግዱ ለእግዚአብሔር በዓ ፀደ መቅደሱ ሲል አዞናልና ።

ሰው፣ በመሠረቱ ግቢ ቅዱስ ሕግ ነው "ክቡር አውስቦ በኩሉ ወዕ[illegible]ከቦ ሙኒ እልቦቱ ስዕበት ተብሎ [illegible]ፉ ልና ዕብ ፲፫ ፣ ፬

# ዜና ሊቃውንት

## በድጓና በአቋቋም መምህርነት የታወቁት ሊቅ የመልአከ ፀሐይ ዘለቀ አጭር የሕይወት ታሪክ

በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ደብረ ብርሃን ከተማ አጠገብ ላንጃ ግንድ ጊዮርጊስ ከአባታቸው ከአለቃ ሀብተ ማርያም ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ በ፲፰፻፹፬ ዓ/ም ኅዳር ፳፬ ቀን ተወለዱ

ለትምህርት ሲደርሱ ጊዳ ወረዳ ጋል ይ በሚባል ቀበሌ ደብረ ሐመልማል ከመሪጌታ ክንፉ ዘንድ ንባብና ዳዊት ተማሩ ።

ከዚህ በኋላ ወደቁንዲ ጊዮርጊስ በመ ሔድ ከመሪጌታ ባንቴ ይዋሉ ዘንድ ተ ጉለቴ ዜማን በሙሉ አጠናቀው ተማሩ ከዚህ ቀጥለው የተጉለቴውን ዜማ ትተ ው ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሄድ

የቤተ ልሔም የድጓ መምህር ከነ በሩት ከመሪጌታ ወልደ ቂርቆስ ዘንድ እንደገና ሰላም ለኪ ብለ ው ጾመ ድጓ ምዕራፍና ድጓ በሚገባ አጠናቀው ተማሩ ። በድጓ መምህርነት አስመስክረዋል ።

ከዚያም ወደ ጐጃም ሔደው ድማኅ ጊዮርጊስ ከአለቃ ዕንቁ ቅኔ ተምረው ዳግመኛ ወደ ደብረ ሊባኖስ ተመል ሰው ከመምህር አምኃ ዘንድ የቅኔን አገባብና ቅኔን አጠናቅቀዋል ።

ከዚያም 2ኛ ከመሪጌታ ወልደ ቂር ቆስ ተመልሰው የድጓን ይትበሃልና ቁም ዜማ እየተማሩ ተቀምጠው ሳሉ እኒሁ መምህራቸው ወደእንጦጦ መን በረ ፀሐይ ማርያም ሲመጡ አብረው ተከትለው መጥተው በአቋቋም መምህ ርነት ከታወቁት ሊቅ ከጐንደሬው ከ መልአከ ፀሐይ አፈወርቅ ዘንድ አቋቋ ም በሚገባ ተምረው በአቋቋም መምህ ርነት ተመረቁ ። በዚያን ጊዜ የእንጦጦ ከተማ አዲስ ትክል በነበረችው በመን በረ ፀሐይ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዕቴጌ ጣይቱ ብጡል የመልአከ ፀሐይ ዘለቀን ድምፀ መልካምነትንና ሊቅነ ትን ተመልክተው የቀኝ ጌታ መዘምር ሁነው እንዲያገለግሉ በደብተርነት ተ ከሏቸው ።

ከዚያ ቀጥለው ጐልቶ አንድ ጋሻ ምርጥ መሬት በርስትነት ሰጧቸው ። በተጨማሪም ሜታ ወረዳ የኑሮ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መርጌታነት ተሸመዋል ። ታላቁ ሊቅ መልአከ ፀሐ ይ ዘለቀ በትጋታቸውና በብልህነታቸ ው ከደቀ መዝሙርነት ወደ መምህር ነት ደረጃ ደርሰው በአቋቋም መምህር ነት ስለተመረቁ ወንበር ዘርግተው ተማሮቻቸውን በግል ሀብታቸውና ን ብረታቸው በልብስ በቀለብ እየረዱ ማስተማር ጀመሩ ።

በተጨማሪም በዕቴጌ ጣይቱ ብጡል መልካም ፈቃድ የእንጦጦ መንበረ ፀሐይ ማርያም ርእሰ ደብር ሁነው ተሹ መዋል ።

የመምህርነት ተግባራቸው በማደጉና ደቀ መዛሙርቶቻቸው ስለበዙ ሰንዳፋ ወረዳ በረህ ቀበሌ ለመምህራንና ለተ ማሮች መተዳደሪያ ይሆን ዘንድ ለቤተ ክርሳቲያኒቱ የተፈቀደ መልከኝነት ተሰጥቶአቸዋል ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ከፋሽሽት ጋር በተደ ረገው ጦርነት ማይጨው ዘምተው ግዳ ጃቸውን ፈጽመዋል ስለኢትዮጵያ ነፃ ነት በጾም በጸሎት ሁነው እግዚአብሔ ርን እየለመኑ ቆይተዋል ።

በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም በብፁዕ አቡነ አብር ሃም መልካም ፈቃድ በርእሰ ደብርነት በተሾሙበት በመንበረ ፀሐይ ማርያም አለቃ ሁነው ተሹመዋል ።

ከዚያም ከኢትዮጵያ ነፃነት በኋላ በመንግሥት ፈቃድና በእጨጌ አቡነ ባስልዮስ ትእዛዝ መልአከ ፀሐይ ዘለቀ ተብለው ተሹመዋል ።

በዚህ ታላቅ ማዕርግ በነበሩም ጊዜ የአቋቋም መምህርነቱንም ሳያቋርጡ በትርፍ ሰዓታቸው ያስተምሩ ነበር ።

በአቋቋምና በድጓ መምህርነታቸው ም ብዙ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስረክ በዋል ።

መልአከ ፀሐይ ዘለቀ ሊቅነታቸው በዜማ ብቻ ሳይሆን ብራና ፍቀው ብዕር ቀርጸው ቀለም በጥብጠው የቁም ጽሕ ፈት ሞያም ነበራቸው ሐረግና ሥዕ ልም በጣም ይችሉ ነበር ።

ቀመረ ዐረብና አቡሻህር ጠንቅቀው የሚያውቁም ነበሩ ። ሊቁ መልአከ ፀሐይ ዘለቀ አርቆ አስተዋይ የንግግርና የጨዋታ ዘዴና ፈሊጥ የሚያውቁ ስለ ነበር ። በቤተ መንግሥትም በቤተ ክህነ ትም በጣም ይወደዱ ስለነበር ከእንጦጦ ወደ ቤተ መንግሥት ለሥራ ጉዳይ ሲ መጡ ልዩ የማረፊያ ቤት ይሰጣቸው ነበር ። በሕግ መወሰኛም ተመድበው ሠርተዋል ። ሊቁ መልአከ ፀሐይ ዘለቀ በማኅሌት መካከል መቋሚያቸውንና ጸናጽላቸውን ይዘው ሲዘሙና ሲጸነጽ ሉ ለተመለከታቸው ሁሉ እጅግ ደስ ያሰኙ ስለነበር የመልአከ ፀሐይ ዘለቀን ማኅሌት ለማየት የሚጓጓውና የሚመ ኘው ሕዝብ እጅግ ብዙ ነበር ስማቸውን የሚያስታውሱ ፲፱ ልጆችች ወልደዋል ።

ሊቁ መልአከ ፀሐይ ዘለቀ ብዙ ዘመ ን በሥጋ ወደሙ ከተወሰኑ በኋላ ከዚያ ም በ1954 ዓ/ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እጅ ማዕርገ ምንኩስና ተቀብለዋል ።

ከዚህ ቀጥለው በመንግሥት ፈቃድ ወደቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሔደው ቅዱሳት ገዳማትንና መካናትን እንዲ ሁም የግብፅን ገዳማት ተሳልመው መጥተዋል ።

መልአከ ፀሐይ ዘለቀ በተወለዱ በ ፹፯ ዓመታቸው በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ጥር አን ድ ቀን በድንገት አርፈው ሊቃነ ጳጳሳት ና ኤጲስ ቆጶሳት የአዲስ አበባ ከተማ አድባራትና ገዳማት አለቆችና ሊቃው ንት በተገኙበት በእንጦጦ መንበረ ፀሐ ይ ማርያም በታላቅ ማዕርግ የቀብራ ቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

የታሪኩ አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል ተስፋ ዘገነት ማርያም ።

ተጋቢዎች ሥርዓተ ጋብቻቸውን በሚፈፅሙበት ጊዜ እስከ ፯ ቀን ድረስ የተከለከሉበት ምክንያት በጫጉላው በተድላና በደስታ ስለሚሰነብቱ ነው ።

፭ኛ/ ጥያቄ ሙሽራውን አጅበው ሲመጡ ደረታቸውንና ጡታቸውን እያ ሳዩ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸ ውን እኛም ተገቢ ነው ብለን አንቀበ ለውም እንዲያውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሴቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ራሳቸውን ይከናነቡ ያለው እንደ ዚህ ካለ ነገር እንዲጠበቁ ለማስገን ዘብ ነው ።

ስለዚህ ተክሊል በሚፈጸምበት ጊዜ ግማሽ ሰውነታቸውን ለብሰው ግማሽ ሰውነታቸውን ሳይለብሱ ለሚመጡት ሁሉ ማስተማር ያስፈልጋል የሚሽራን ልብስ ለብሶ መምጣት እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ግማሽ ሰውነትን አራቁቶ አድርጎ መግባት አይገባም ።



www.ethiopianorthodox.org

# "አንደበት እሳት ናት"

የሰው አካል ከራስ ጠጉሩ ጀምሮ እስ ከ እግር ጥፍሩ ድረስ ያለው አቅዋም አ ንድ አካል ቢሆንም በውስጡ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የአካል ክፍሎች አሉት

ከብዙዎቹም ክፍሎች አንድዋ አን ደበት ናት ፣ አንደበት ስናያት ከሁሉ የለሰለሰች አጥንትና ጅማት የሌላት ከመሆንዋም በላይ መትታ የምታሳም ም ደብድባ የምትገድል አትመስልም ነገር ግን አንደበት ለስላሳና ደካማ መ ስላ ትታይ እንጂ ከሁሉ የበለጠ ኃይል አላት ይኸውም ሥጋን ቆርጣ አጥንትን ከማድቀቋም ሌላ ሀገርን ታቃጥላለች ።

ሁሉን ያየና የብዙ ሥነ ፍጥረቶችን ኃይል የተመለከተ ሐዋርያው ያዕቆብ ም የአንዱን ኃይል ከሌላው ኃይል እያ ነጻጸረ በሚናገርበት ጊዜ ፈረስ እንዲታ ዘዝልን በአፉ ልጓምን እናስገባበታለን ፈረሱንም ወደ ፈለግነው ቦታ እንመራ ዋለን ፣ መርከብም ምንም ትልቅ ቢሆ ንና በትልቅ ነፋስም የሚነዳ ቢሆን የመ ርከቡ ነጂ በትንሽ መሪ ወደፈለገው ቦታ ይነዳዋል ካለ በኋላ የአንደበትን እሳትነት ሲገልጽ የሚከተለውን ጽፎ እናገኘዋለን ።

"አንደበት ትንሽ የአካል ክፍል ስት ሆን በታላላቅ ነገሮች ትመካለች ትልቅ ጫካ የሚቃጠለው በትንሽ እሳት ነው፣ አንደበትም እሳት ናት ብሏል ሐዋርያ ው ነገሩን በማራዘም (ምላስ) አንደበት በአካል ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት ሥጋችንንም ሁሉ ታረ ክሳለች ሰውነታችንንም ታቃጥላለች ሲል በሰፊው ተንትኖ አስረድቷል ያዕ ፫-፮ ።

ሐዋርያው ያዕቆብ እንደተናገረው አንደበት ምንም እንኳን ለስላሳ ብትሆ ን ደካማ መስላ ብትታይም እሳት ከሚ ያቃጥለው ቃጠሎ ባላነሰ ኃይል እንደ ምታቃጥል እነሆ ሐዋርያው ያዕቆብ አ ረጋግጧል በአንደበት ያልቆሰለ ሰው ማን ነው በአንደበትስ አንጀቱ ያላረረ

ማን ነው ?
እንዲያውም ጠቢቡ ሲራክ የአንደበ
ትን እሳትነት ሲገልጽ እንዲህ ብሏል
(ብዙኃን እለወድቁ በኩናት ወእኮ ከመ
እለ ወይቁ በልሳን) ስለ ሀገር ፍቅር ፣
ስለ ወገን ክብር ፣ ሀገርን ለመጠበቅ ድ
ምበርንም ለማስከበር እግራቸውን ለጠ
ጠር ደረታቸውን ለጦር ሰጥተው ውድ
ሕይወታቸውን የሰጡ እጅግ ብዙ ናቸ
ው ።

ነገር ግን ከእነዚህ ይልቅ በነገረ ሠ
ሪና በውሸት በአንደበት እሳትነት የጠ
ፉ ይበዛሉ ሲል የአንደበትን እሳትነት
ግልጥልጥ አድርጎ ተናግሯል ፣ አዎ አን
ድ ሰው በዱላ ሲደበደብ በድንጋይ ሲወ
ገር ሰውነቱ እንደሚቆስልና አካሉ እን
ደሚቆራረጥ ሥውር አይደለም ።

ይሁን እንጅ የቆሰለው ሰውነት በሕ
ክምና እና በልዩ ልዩ መድኃኒት የቆሰ
ለው ይድናል የተሰበረው ይጠገናል ፤
እንደቀድሞው ፍጹም ጤናንም አግ
ኝቶ ሊኖር ይችላል ነገር ግን በምላስ የ
ቆሰለና በአንደበት የተደበደበ አካል ፈ
ጽሞ ቁስሉ ሊድንና ስብራቱ ሊጠገን
አይችልም ።

እንዲያውም አንድ ገጣሚ ይህንን አ
ስመልክቶ የገጠመውን ግጥም ብገልጥ
ላችሁ ለስነ ጽሑፍ ተስማሚ መስሎ ስለ
ታየኝ መልካም ነው ግጥሙ "ቢቆስል
ም ይድናል የተደበደበ ፣ (አንደበት) ም
ላስ ግን ይኖራል እንዳንገበገበ "፣
ብሏል እርግጥ አሁንም ቢሆን የቆሰለ
ሰውነት ባንድ ጊዜ ድኖ እንዳልነበረ ሲ
ሆን በአንድበት የቆሰለ ሰውነት ግን
ከእሳት እንደገባ ጅማት አንጀትን ሲያ
ቃጥል ነው የሚኖረው በአንደበት የሚ
ያያዘውን እሳትነት የተገነዘበ ዳዊትም
ከዚሁ ነፃ ሁኖ እንዲገኝ እቤ አዐቅብ አ
ፉየ ከመ ኢደስሐት በልሳንየ በአንደ
በቴ እንዳልስት አፌን እጠብቃለሁ ብ
ሏል ።

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ
ነፃ ሁኖ ለመገኘት እንደእነ ዳዊት አፍ
ን መጠበቅ ነው ።

ከፉ ነገርን መወርወር በአንደበት እ
ንደፈለጉ መናገር ውጤቱ ጥፋትና ሐ
ዘን ነው ። አንድ ፈላስፋ እንደተናገረ
ው ዓለም ወረተኛ ናት ለቀደሙ ሰዎች
እንዳልነበረችላቸው ለእኛም አትኖርል
ንም ።

ስለዚህ ከስሕተት ንጹሕ ሁኖ ለመ
ኖር የሚፈልግ ሰው ሁሉ አንደበቱን ይ
ጠብቅ አንደበቱን ከጠበቀ የአንደበት
እሳትነት ሊያገኘው አይችልምና ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

# ሃያ አራት ሽማግሌዎች

ሽማግሌ የሚለው ቃል በሁሉም ዘ
ንድ የታወቀ ቢሆንም የተለያየ አጠራር
እንዳለው ማወቅ ይገባናል ከኅብረተሰ
ቡ መካከል አንዱ ሽማግሌ ስለሚለው
ቅጽላዊ አጠራር ላረጁና ላፈጁ አባቶች
ብቻ የተሰጠ ይመስለዋል ሌላው ደግ
ሞ ነገር ለሚዘነጉ ፣ ጠባያቸው ወደ ሕ
ፃንነት ለተለወጡ አረጋውያን ብቻ የ
ተሰጠ ስያሜ አድርጎ ይቆጥረዋል እኩ
ሉ ደግሞ በእርጅና በሽምግልና ዳኝነት
የተያዙት አዛውንት በሚመለከትበት
ጊዜ የራሱን ውርዝውና ለዘለዓለም እን
ደሚኖር አድርጎ በመቁጠር አረጋውያ
ኑን ይንቃል ያቃልላል በዘመናችን አን
ዳንድ ልጆች ሽማግሌዎችን ሽሜ ጉጉ
እያሉ እንደሚሳደቡት ሁሉ በልባቸው
ሽማግሌዎችን የሚያንቋሽሹ ሰዎች እን
ዳሉም የታወቀ ነው ።

ሽማግሌን በሽምግልናው (በአረጋ
ዊነቱ) የሚገባውን ክብር እየሰጡ እኔም
እኮ ነገ እንደዚሁ ነኝ እያሉ በፈሪሃ እግ
ዚአብሔር የሚኖሩም ብዙዎች ናቸው
በመሠረቱ ሽማግሌ ማለት ምን ማለት
ነው ? ግዕዛዊ አማርኛ "መልሕቅ ብሎ
ሊቅ ፣ ታላቅ የሚበልጥ ፣ አለቃ ሹም
አሮጌ ሽማግሌ " ይልና ማስረጃ ሲሰጥ
"መላህቅተ ሕዝብ" "የሕዝብ አለቆ
ች በማለት ስለሽማግሌዎች ምንነት ያ
ስረዳል ከዚህ በላይ ባነበብነው ውስጥ
ሽማግሌ የሚለው ቃል በመጨረሻ ላይ
ብቻ እንደተጠቀሰ አንበናል " በዝርዝ
ር ስንመረምረው ግን ሽማግሌ ማለት
የተማረ አዋቂ አስታራቂ ተመራማሪ
አስተዋይ ብልህ ከነዚህ ሁሉ የላቀ የበ
ለጠ እነዚህን በተግባር የሚተረጉም በ
አጠቃላይ ችሎታው ተመዝኖ ወይም
በሁሉም ዘንድ ታውቆ የሁሉ አለቃ ለ
መሆን የበቃ ማለት ነው ።

እንደነዚህ ያሉት ሽማግሌዎች በሁ
ሉም ዘንድ ይፈለጋሉ ሽማግሌዎች አብ
ዛኛዎቹ ብልጫ የሚያሳዩት በዕድሜ
የበሰሉ ናቸው በዚሁ ሥራ የታወቁ ሽ
ማግሌዎች ሕብረተሰቡን እያስማሙ እ
ንዲመሩ በመንግሥታቸው እየተመረ
ጡ የሚሰሩ በእብራውያን ዘመን እንደ
ነበሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመለከታለን
"ሙሴንም አንተ አሮንም ናዳብም አብ
ዩድም ከእስራኤልም ሰባ ሽማግሌዎች
ወደእግዚአብሔር ውጡ በሩቅም ስገዱ
ይላል እንዲሁም "ሙሴም ወጣ የእግ
ዚአብሔርንም ቃሎች ለሕዝቡ ነገረ ከ
ሕዝቡ ሽማግሌዎች ሰባውን ሰዎች ሰብ
ስቦ በድንኳኑ ዙሪያ አቆማቸው " የሚ
ል ቃልም እናነባለን (ዘፀአ ፳፬ ፣ ፩ ፣ ዘ
ኁል ፲፩ ፣ ፳፬ ።)

በሀገራችን በኢትዮጵያም በምግባረ
ሠናይ የታነፁና በኅብረተሰቡ ዘንድ የ
ታወቁና የተወደዱ በየክፍለ ሀገሩ እንደ
ነበሩ ይነገርላቸዋል በዘመነ መሣፍንት
በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን አው
ራጃ ከኅብረተሰቡ መካከል በዕድሜአ
ቸው በቁመናቸውና በዘራቸው ሳይሆን
በግብረገብነታቸው በጠባያቸውና በአስ
ተዋይነታቸው በሕዝቡ ተመርጠው ሕ
ዝቡን በሰላም የሚመሩና የሚያስተዳድ
ሩ ሰባ ሽማግሌዎች ነበሩ እነዚህም ሽማ
ግሌዎች የራሳቸውን ጥቅም ከማስቀደም
ይልቅ የሕብረተሰቡን ፍላጎት በማስቀ
ደም ሰላምና ፍቅር በሕብረተሰቡ እን
ዲሰፍን ያደርጉ ነበር ።

እነዚህ ሽማግሌዎች በአንድ ሥፍራ
ሳይቀመጡ ከአውራጃው ርእሰ ከተማ
ወደ ወረዳዎቹ ሁሉ እየሄዱ የተጣሉትን
በማስታረቅና በማስማማት የተራራቁ
ትን በማቀራረብ የተቸገሩትንም የሚረ
ዱበትን መንገድ እያጠኑ ችግሩ ከኅብረ
ተሰቡ መካከል እንዲጠፋ ያደርጉ ነበር
በዚሁ ተልእኮአቸው እንዳሉም አንድ
ችግር አጋጠማቸው ይኸውም ችግር
እንደአገሩ ልማድ አንዲት ልጃገረድ
በሬ ፣ ላም ከሌላት ባል ለማግኘት አት
ችልም በዚህ ምክንያትም ብዙ ያላገቡ
ትላልቅ ልጃገረዶች ተመለከቱ ።

ሁኔታውን ለመረዳት ያላገቡበትን ም
ክንያት ጠየቁ ያገኙት መልስ ግን በሬ ፣
ላም የላቸውም ስለዚህ በቁም ቀሪዎች
ስም ሲጠሩ ይኖራሉ አሉአቸው እነርሱ
ም ይህንኑ ችግር ለማስወገድ ምክክር
ያዙ ከብዙ ውይይት በኋላም በተምቤን
አውራጃ ያሉ ባለጸጎች እያንዳንዳቸው
አንድ አንድ ጊደርና አንድ አንድ ወይ
ፈን መስጠት እንደሚገባቸው በትምህ
ርትና በማግባባት ልብን በሚነካ ንግግ
ር አሳመኑአቸው በዚሁ ዕቅዳቸው ሁሉ
ም ሀሳባቸውን ስለተቀበለው ብዙ ጊ
ደሮች ላሞችና የጋማ ከብቶች አገኙ ከ
ዚህ በኋላ በአውራጃው ያሉትን ልጃገረ
ዶች በሙሉ ሰብስበው አከፋፈሉአቸው
ልጃገረዶቹም እንደ ባለጸጎቹ ልጆች
ባል ለማግባት እንደበቁ ይተረካል። ሽ
ማግሌዎቹንም በዚሁ የተቀደሰ ዓላማ
ቸው ያየና የሰማ ሁሉ ይኖሩበት የነበረ
ው ቦታ "ዓቢይ ዓዲ" ታላቅ ሕዝብ የ
ሚኖርበት ታላቅ አገር ብለው ስለሰየ
ሙት የዚሁ አውራጃ ርዕሰ ከተማ እስ
ካሁን ድረስ በዚሁ ስም ሲጠራ ይኖራል
በዘመናችንስ ሽማግሌዎች ይኖሩ ይ
ሆን ? ማለት ከላይ እንደተጠቀሱት ያሉ
በሁለት ወንድማማች መካከል የተፈጠ
ረውን ጠብ አብርደው ሰላም ፍቅርና
ወንድማማችነትን የሚመሠርቱ አሉ ?
በባልና ሚስት መካከል የጠፋውን ሰላ
ምስ አብርደው አስተራርቀውና የሞቀ
ትዳራቸውንም በበለጠ አደራጅተው
እንዲኖሩ የሚያደርጉ ሽማግሌዎች ይገ
ኛሉ ? ካሉ መልካም ነው ከሌሉ ግን እ
ባቶቻችን በሀገር ወይም በመንደር ጠብ
ሰፍኖ ሲመለከቱ በሀገሩ ላይ ሽማግሌ
የለም ? እያሉ በመገረም ይናገሩ እንደ
ነበረ መገረማችን አይቀርም ።

ወደ መሠረተ ሀሳባችን እንመለስና
"ሃያ አራት ሽማግሌዎች " ስለሚለው
የጽሑፋችን ርእስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እ
ንመልከት በራእየ ዮሐንስ ፬፣፬ በዙፋኑ
ዙሪያ ሃያ አራት ዘፋኖች ነበሩ በዘፋኞ
ቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸ
ውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሃያ እ
ራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር
ይልና እልፍ ብሎም "ሃያ እራት ሽማግ
ሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት
ወድቀው ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በ
ሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ ጌታችንና
አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃ
ልና ፈቃድህም ሆኖዋልና ተፈጥረውማ
ልና ክብር ምስጋና ለአንተ ይገባሃል እ
ያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራ
ሉ" ይላል ከዚህም በመቀጠል በዙፋኑ
እና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽ
ማግሌዎችም መካከል እንደታረደ በግ
ቆሞ አየሁ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓ
ይኖች ነበሩት እነርሱም ወደምድር ሁሉ
የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ና
ቸው " ሲል ያየውን ጽፏል ።

ጥቅሶቹ ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ቻ
ይነትና ስለፍጥረታት አስገኝነቱ ለዚሁ
ም ገናናነቱ መላእክት ክብርና ውዳሴ
እያቀረቡለት አክሊላቸውንም ከራሳቸ
ው እያወረዱ እንደሚሰግዱለት በግ
ልጽ ያስረዳል ከጥቅሶቹ መካከል እነ
ርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚ
አብሔር መናፍስት ናቸው" የሚል
ቃል እናገኛለን ።

ግንዛቤአችን እንደሚያስረዳን ምድ
ራውያን ሽማግሌዎች ለምድራውያን
ወንድሞቻቸው የሚያደርጉላቸው እን
ክብካቤ ከዚህ በላይ ከሙሉ በክፍሉ እ
ንደተጠቀሰው ሁሉ የሃያ አራቱ ሽማግ
ሌዎች ተግባርም ስለሰው ልጆች ደህን
ነት በተለይም ምድራውያን ሰዎች ከፈ
ጣሪያቸውና ከአምላካቸው ከእግዚአብ
ሔር በተጣሉና በኃጢአታቸው ምክንያ
ት በተለዩ ቁጥር በተሰጣቸው የእሥታ
ራቂነት (የሽምግልና) ሥልጣን ሌት ተ
ቀን ሲያማልዱን የሚኖሩ ቅዱሳን መላ
እክት መሆናቸውን ያስረዳናል ።

እነዚህ ሃያ አራት ሽማግሌዎች በግ
ዕዝ እስራ ወአርባ እቱ ካህናተ ሰማይ ይ
ባላሉ እንደግዕዙ አባባል ሽማግሌ የሚ
ለው ቃል ካህን (ቄስ) ማለት ነው ።ካህ
ናቱ (ሽማግሌዎቹ ) ሕብረሥራው የማ
ይታወቅ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሁኔታ
ውን ለመግለጽ ተመሳሳይ የማይገኝለት
አክሊል ደፍተው የወርቅ ጽንሐሕ ይዘ
ው በመንበረጸባዖት ዙሪያ ሆነው ቅዱስ
ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍ
ጹም ምሉእ እያሉ ሃያ አራት ሰዓት እን
በለ አጽርኦ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ
የሚኖሩ ናቸው ።

ከእምልኮተ እግዚአብሔር ርቀው
ከምግባር ከሃይማኖት ተራቁተው በዚ
ህ ዓለም የሚቅበዘበዙትን ሰዎች ሁሉ
መክረው አስተምረው በንስሐ አድሰው
በሥጋው ወደሙ አጽተው ከፈጣሪያ
ቸው የሚያስታርቁ ምድራውያን ሽማ
ግሌዎች ካህናት ስለሆኑ በእሥራ ወአር
ባዕቱ ካህናተ ሰማይ ተመስለዋል ።

ታድያ ይህን ትልቅ ማዕርግና ሥል
ጣን እንደወርቅና እንደ እንቁ መጠበቅ
ይገባል ። እሥራ ወአርባእቱ ካህናተ ሰ
ማይ ወይም ሃያ አራት ሽማግሌዎች ፈ
ጣሪያቸውን እንበለ አጽርኦ ቅዱስ ቅ
ዱስ ቅዱስ እያሉ ዘለዓለም ዓለም ሲ





www.ethiopianorthodox.org

# የትንቢትና ምሳሌዎች ትርጉም ዓምድ

አዘጋጅ መ/አ መክብብ አጥናው

መላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በትክክል ለማስተዋል ምሳሌዎችንና ትንቢቶችንም ለመተርጐም የሚያስችል በቂ ዕውቀትና ልምድ መኖር አለበት። ትንቢትና ምሳሌዎችን ተርጉሞ የመገንዘብና የማስረዳት ችሎታ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን መካከል ያለውን አንድነት (ግንኙነት) በትክክል ለማስተዋል ይረዳል ። ይኸውም ሁለገብ የሆነ ዓይነተኛ ቁልፍ በአንድ ሕንፃ ውስጥ የሚገኙ በሮችን ሁሉ ያለምንም ችግር ለመክፈት እንደሚያስችል ትንቢትና ምሳሌዎችንም ተርጉሞ የመረዳት ልምድ ልክ እንደዚሁ ነው ።

ታዲያ ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የስብከት ዘዴ መመሪያ መጽሐፍ ዋናዓላማና ተግባር በብሉይ ኪዳን ተጽፈው የሚገኙትን ትንቢትና ምሳሌዎችን ከሐዲስ ኪዳን ጋር በማገናዘብ መተርጐምና ማስረዳት ነው ።

በመሠረቱም ምሳሌዎችና የሥዕላዊ ታሪክ ማስረጃዎች ሁሉ ትንቢታዊ ይዘት አላቸው ። ስለዚህ የምሳሌዎች አነጋገር ሁሉ በትርጉም ሰንሰለትነት ከትንቢት ጋር ተጣምሮ ወደ መሢሕ--- ክርስቶስ አመጣጥ የሚያመለክት ቀስት ነው ።

ምሳሌነት ያላቸው ንግግሮች ሁሉ እጅግ ውብ ከሆነ አስደናቂ ታሪኮችና ቅኔዎች ጋር በመጐዳኘት በሰዎች ልብና አእምሮ ውስጥ ሠርፀው በሕያውነት የሚኖሩ ናቸው ።

ምሳሌያዊ አነጋገር በጥንታውያኑ የመካከለኛው ምሥራቅና የሩቅ ምሥራቅም አህጉር ሕዝቦች የተለመደ መሠረታዊ ይትባሃል በመሆኑ ምክንያት የብሉይ ኪዳን ፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የተተረጐሙት ታሪክና ምሳሌዎችን እንደ ሥዕላዊ ማስረጃ አድርገው ምሥጢራትን በማጉላት ነው ። ምሳሌዎች ከትንቢት ጋር ተቀናጅተው ሲቀርቡ ልብን የሚመስጥ (የሚማርክ) ውብ የአገላለጥ ጥበብ አላቸው ።

ስለዚህም ለስብከተ ወንጌል ተልዕኮ አፈጻጸም ፣ ለሰንበት ት/ቤትና ለካህናት ማሠልጠኛዎች ማዕከላት በአስተማሪነት ሥራ ላይ የሚመደቡ መምህራንም ሆኑ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቀድሰው ለሚያቆርቡ የተመረጡ ካህናት የሚያነቡትን ወንጌል ተርጉመው ለማስተማር በሚዘጋጁበት ወቅት ሁሉ ከዚህ የትንቢትና ምሳሌዎች ትርጉም መሠረታዊ የትምህርትና የስብከት ንድፈ ሐሳብ ማግኘት ይችላሉ ።

ለማንኛውም የመንፈሳዊ ትምህርት መስጫ ማዕከል በአስተማሪነት ለሚያገለግሉ ካህናት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የስብከት ዘዴ መመሪያ ይሆን ዘንድ በአስተዋፅኦ ትርጉም የተሰናዳ ይህ የምሳሌዎች ምርምርና የትንቢት ትርጉም መድብ (ስብስብ ሥራ)ወይም ከምችት ከ፳፭ ዓመታት በላይ በተራዘመ ጊዜ ውስጥ ብዙ መጻሕፍትን ከማንበብ የተገኘ ውጤት ነው ። ጠቅላላ መልእክቱም ሁለገብ ነው ።

የዝግጅቱም ዋና ምንጭ በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤት ክርስቲያን ሊቃውንት የአንድምታ ትርጉም መጽሐፍ ቢሆንም በልሳነ እንግልጣር ከተጻፉ አያሌ የትርጉም መጻሕፍት የተመረጡ ሐተታዎችም ታክለውበታል ።

ከዚህም የተነሣ ለዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ አንድነት እንቅስቃሴም አስተዋፅኦ ያለው እንዲሆን አቅም የፈቀደውን ያህል ጥረት ተደርጎበታል ።

አሁንም የብዙ ዕውቀት ጸጋና በረከት የሞላበት ይህ ሐዲስ ዓለማችን ክርስቲያናዊ አንድነት ፣ ፍቅርና ሰላም የሠፈነበት እንዲሆን የሰላም ባለቤት እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን ።

## በብሉይ ኪዳን የተጻፉ ምሳሌዎች

"ምሳሌ" የአንድን ነገር ምንነት እንደ ሥዕላዊ ማስረጃ ወይም እንደ መነፅር አጉልቶ መንፈሳዊ ምሥጢርን ለመተርጐምና ዕውነትን ለመገንዘብ የሚያስችል መግለጫ ማብራሪያ ነው።

"አምሳል" የሚለው ቃል ደግሞ የምሳሌ ብዛት ነው ። ነገር ግን እንደልማድ ሆኖ በነጠላነትም ይነገራል ። (፩) በልሳነ እንግልጣር አምሳል (ምሳሌ) ለተሠኘው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ "ታይፕ" ማለት ነው ። ታይፕ የሚለውም ቃል በልሳነ ጽርዕ (ግሪክ) "ቲፖስ" ከተሠኘ ቃል የተወረሠ ነው ። ትርጉሙም ወደፊት ለሚሆን ድርጊት ወይም ዘግየት ብሎ ለሚመጣ ለአንድ አማናዊ ድርጊትም ሆነ ወይም ነገር ፣ወይም ለአንድ አስፈላጊ ሰው እንደጊዜያዊ ምትክ የሆነ ወኪልነት ያለው ቃል ወይም ታሪክ የሚገለጥበት ማስረጃ ማለት ነው ።

ለምሳሌ ኦሪት ወይም የብሉይ ኪዳን ሕግ ለሕገ ወንጌል (ለሐዲስ ኪዳን)አምሳል ነበር ። ምሳሌ ወይም አምሳል ትንቢትነት ያለው እንደመሆኑ መጠን አፈጻጸሙ በተግባር ጐልቶ የሚታየው ለጊዜው በምሳሌነት የቆየውን አንድ ነገር ወይም ድርጊት የሚተካው ሌላ አማናዊ (ዕውነተኛ) የሆነ ቀዋሚው ነገር ወይም ድርጊት ወይም ሰው የዚያን የጊዜያዊውን ወኪል ቦታ ይዞ ሲገኝ ነው ። ለማስረጃም ያህል በኦሪታዊው የብሉይ ኪዳን ዘመን ይቀርብ የነበረውን የሌዋውያን መሥዋዕት ሁሉ የሚተካው አማናዊው ቀዋሚውና ዘላቂው መሥዋዕት በቀራንዮ መስቀል ላይ የሚቀርበው የክርስቶስ ሥጋና ደም መሆኑን በመላው ዓለም የሚገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ መተርጐማን ገልጠውታል ።

የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ፈርዖናች ባርነት አገዛዝ ነፃ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር (ከንዓን) መግባታቸው በክርስቶስ ደም የተዋጁ ምዕመናን ከሰይጣን ዲያብሎስ ቁራኛነትና ከኃጢአት ባርነት ነፃ ሆነው ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ነበር ።

ምሳሌን ወይም አምሳልን የሚያጅቡ ሌሎች ቃላት ደግሞ አሉ፣እነርሱም መርገፍ ፣ ጽላሎት (ጥላ) እንዲሁም ንድፍ የተሠኙት ናቸው ።

፩. መርገፍ

የቤተ ክርስቲያንን ጉልላት ወይም የጣሪያውን ክፈፍ ወይም የመሶበ ወርቅን መክደኛ ዙሪያ ለማስጌጥ እንደ ጆሮ ጉትቻ ሆኖ የሚሠራ አጫዋች ነው ። ታዲያ መርገፍ የሚያስፈልገው ለጌጥነት ብቻ ስለሆነ መርገፉ ቢኖርም ቤተ ክርስቲያኑም ሆነ መሶበ ወርቁ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ የእግዚአብሔርም ቃል በምሳሌም ያለምሳሌም ሊነገር እንደሚችል ያስገነዝባል ። ለአንድ ኩታ ጥለት የሚያስፈልገው በጌጥነቱ ውበት ለመጨመር ብቻ ነው ሮንዜውም (ያለጥለት ማለት ነው) ሊለበስ ይችላል ። እንዲሁም ለአንድ ቃል ወይም ለአንድ ድርጊት ምሳሌ የሚያስፈልግበት ምሥጢሩን ለማጉላት ብቻ ነው እንጂ ያለምሳሌም ሊተረክ ይችላል ።

፪. ንድፍ

አንድ ዓይነት ሥዕል በሚሠራበት ጊዜ ቀለም ከመግባቱ በፊት የሥዕሉ ቅርፅ በእርሳስ ይነደፋል ። ቅርጹም ከተስተካከለ በኋላ ቀለም በሚቀባበት ጊዜ የእርሳሱ ንድፍ ቦታ እየለቀቀ ቀለሙ እየደመቀ ፣ እያሸበረቀ መጉላት ይጀምራል ።

እንዲሁም በብሉይ ኪዳን የተፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ ለሐዲስ ኪዳን ድርጊቶች እንደ ንድፍ ሆነው የቆዩ ነበሩና ተፈላጊነታቸው የእርሳሱን አገልግሎት ያህል ብቻ ነበር ።

፫. ሠም

የቀድሞ አባቶቻችን እንደአሁኑ ዘመን የቅርጽ ማውጫ ማሽን አልነበራቸውም ። አንድ ዓይነት የወርቅ ጌጣጌጥ መሥራት ሲፈልጉ ሠሙን ያቀልጡና ቅርጽ ያወጣሉ ። በዚያም ቅርጽ ላይ ወርቁን አንጥረው ያፈሱበታል ።የተነጠረው ወርቅ ሲደርቅ ሠሙን ቀርፈው ይጥሉትና ወርቁ የሠሙን ቅርጽ ይዞ ይነግል ። ይህም ዘግየት ብሎ ሠምና ወርቅ የተባለውን ቅኔያዊ ምሳሌ ሊወልድ ችሏል ። ስለዚህም ኦሪትን እንደ "ሠም" ወንጌልን ደግሞ እንደ "ወርቅ" አድርገን መመልከት ይቻላል ።

፬. ጽላሎት (ጥላ)

አንድ ዛፍ ወይም ተራራ ወይም ሰው ራሱ ባለበት ቦታ በፀሐይ ብርሃን ጊዜ ጥላ አይለየውም ይህም ማለት አንድ ሰው የትም ስፍራ ቢሄድ ጥላው ይከተለዋል ። ነገር ግን ዘላቂውና አማናዊው አካል ራሱ ሰውዬው እንጅ ጥላው አይደለም እንደዚሁም ቀደም ብለው በብሉይ ኪዳን ዘመን የታዩ ነገሮች የተፈጸሙ ድርጊቶችና የታሪክ ባለቤቶች የሆኑ ሰዎች ሁሉ ወደፊት በሐዲስ ኪዳን ዘመን ለሚፈጸሙት ነገሮችና ድርጊቶች ወይም ለአማናውያን ሰዎች ምሳሌ ፣ አምሳል ፣ መርገፍ ፣ ወይም ጽላሎት ነበሩ የሚል ማስረጃ በብዙ ስፍራ ይገኛል ። ቆላ. ፪፥፲፮ ።

---

ያመሰግኑ ከመኖራቸውም በላይ የሰው ልጆችንም ከፈጣሪያቸው እንዳይርቁ ሲማልዱ ይኖራሉ ።

የካህናትም ተልእኮ ሌሊት በሰዓታት በማኅሌት ቀን በቅዳሴና በውዳሴ ሰውና ሰውን ሰውና እግዚአብሔርን በማስታረቅ ዘመናቸውን ሙሉ በተቀደሰ አገልግሎት ማዋል እንደሆነ ከዚህ ታሪክ በማነጻጸር መረዳት ይቻላል ።

የሃያ አራት ሽማግሌዎች ዓመታዊ ክብረ በዓላቸው ኅዳር ፳፬ ቀን ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን የእነዚህ ቅዱሳን መላእክት ክብረ በዓል በስማቸው በታነፁት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እጅግ ደማቅ በሆነ ሁኔታ ስታከብረው ትኖራለች ስለዚህ በእነዚህ ቅዱሳን መላእክት ስም ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ያጠጣ ቁራሽ እንጀራ ያበላ በረከታቸውና ረድኤታቸው እንደሚያድርበት የታመነ ነውና በዓላቸውን በእውነት እናክብር ።

ሊ.ትጉ ገ/ክርስቶስ

---

# የአዋሳ ካህናት ....

ከገጽ ፮ የዞረ

ተገኙ ሰዓታትና ማኅሌት በመቆም ቅዳሴም በመቀደስ በሰንበት ት/ቤትም የወንጌል ትምህርት በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል በማለት ገልጸዋል ።

ይልቁንም ይላሉ መምህር ኃይለ ሥላሴ ሠልጣኞች ፩ኛ/ ገበሬዎች ፪ኛ/ በዕድሜም ወጣቶች በመሆናቸው በነበራቸው ሙያ ማሻሻያ ትምህርት ሲሰጣቸው በልማትም ሆነ በመንፈሳዊ አገልግሎት በኩል ዕውቀታቸው መሥራት በሚለው መርሆ መሠረት መምህራንና ተማሪዎች በመተባበር በምናወጣው መርሐ ግብር መሠረት ለልማት ሲሰለፉ ሰለቸን ደከመን ሳይሉ ይሠራሉ ብለዋል ።

በመጨረሻም ሠልጣኞቹ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ወደ የሀገረ ስብከታቸውና ወደየአውራጃቸው ሲሰናበቱ ከፍቅራቸው የተነሣ አንገት ላንገት ተያይዘው እየተሳሳሙ በመደሰትና በናፍቆት ይሰነባበታሉ በዚሁ ጊዜም ት/ቤቱ ተማሪዎቹ በየሄዱበት ሁሉ ሥራቸው የተቃና እንዲሆንላቸው ከምኞት ጋር አሰናብቶአቸዋል ። ሲሉ መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው የማሠልጠኛው ርእሰ መምህር ገለጻቸውን ደምድመዋል ።

ሊ/ትጉሐን ገ/ክርስቶስ ኃይለ ማርያም





www.ethiopianorthodox.org

# ዘግይቶ የደረሰን ዜና

የአዋሳ ካህናት ማሠልጠኛ........

በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በርእሰ ከተማው አዋሳ ላይ የተቋቋመው የካህናት ማሠልጠኛ ተቋም ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና መልአከ ምህረት ጳውሎስ ቀጸላ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የሀ/ስብከቱ ሠራተኞችና የአድባራቱ አለቆች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው ታላላቅ የከተማው ነዋሪዎች በተገኙበት ለ፲፪ኛ ጊዜ ያሰለጠናቸውን ካህናት ያስመረቀ መሆኑን የማሠልጠኛው ርእስ መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ በስነ ጽሑፍ ማደራጃ ክፍል ተገኝተው ባደረጉልን ገለጻ ለማወቅ ችለናል።

መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው ስለ ማሠልጠኛው ባደረጉት ገለጻ ቀደም ሲል በማሠልጠኛው ሰልጥነው ይወጡ የነበሩት ካህናት ከባሌ ፣ ከጋሞጎፋና ከሲዳሞ ሀገረ ስብከቶች የተውጣጡ ካህናት እንደነበሩ አውስተው ባሁኑ ጊዜ ግን የጋሞጎፋ ሀገረ ስብከት ራሱን የቻለ የካህናት ማሠልጠኛ ስላለው በአዋሳ የካህናት ማሠልጠኛ ተቋም የሚሠለጥኑ ካህናት የሲዳሞና የባሌ ሀገረ ስብከቶች ብቻ መሆናቸውን አስረድተዋል።


ይህ ማሠልጠኛ ይላሉ መምህር ኃይለ ሥላሴ ከ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ የሁለቱ ክፍላተ ሀገራት ካህናትን በዓመት ሁለት ጊዜ አሠልጥኖ በማስመረቅ ላይ መሆኑን ገልጸው እስከአሁን ያስመረቃቸውን ካህናትም በዝርዝር ሲያስረዱ ፣

ሀ. ከጋሞጎፋ ሀገረ ስብከት ፲፪
ለ. ከባሌ ” ” ፺፱
ሐ. ከሲዳሞ ” ” ፪፻፵፱ ሲ

ሆኑ ከነዚህም ፴፩ መነኮሳት ፪፻፩ ቀሳውስት ፹፰ ዲያቆናት በድምሩ ፫፻፳ መሆናቸውን አመልክተዋል።

መምህር ኃይለ ሥላሴ ይግዛው ሰልጣኞቹ ምን ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚሰጣቸው ላደረግንላቸው መጠይቅ ሲመልሱ ፣

፩. ነገረ መለኮት
፪. ትምህርተ አበነፍስ
፫. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
፬. የስብከት ዘዴ
፭. የቤ/ክርስቲያን ታሪክ
፮. ቃለ ዓዋዲ
፯. ልማትና የመሳሰሉት መሆናቸውንና ይህም ትምህርት ከመደበኛ መምህ



ሠልጣኞቹ ካህናት የሚሠሩት ተግባረእድ

ራን በላይ ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መልአከ ምህረት ጳውሎስ ቀጸላ በየጊዜው ከማሠልጠኛው እየተገኙ ለሠልጣኞቹ ጠለቅ ያለ የቤ/ክርስቲያን ትምህርት እንደሚሰጡአቸውና ተግተው እንዲያጠኑም በምክርና በትምህርት እያበረታቱ ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው በሰፊው አስረድተዋል።

ከዚህም በላይ ብፁዕነታቸው በምረቃው ዕለት ለእያንዳንዳቸው ምክርና መመሪያ ሰጥተዋቸዋል ካሉ በኋላ ከምክርና ከመመሪያውም በከፊል እናንተ በኅብረተ ሰቡ መካከል ስትኖሩ ከሌላው ሕዝብ የተለየ አኗኗር እንድታሳዩ ይገባችኋል ማንም ሰው በሚታይበት ማለት በአልባሌ ቦታ በሚያስነቅፍና በሚያስተች ሥፍራ መገኘት ትልቅ እንቅፋት ስለሚሆንባቸው መጠንቀቅ አለባችሁ ስትመክሩና ስታስተምሩም በጥበበ መንፈስ ቅዱስ እንዲሆን ይገባል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው መመሪያና ትምህርት እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ እናንተ የምድር ጨው ናችሁ የሚለውን ቃል ዘወትር ልታስታውሱት ይገባል እነዚህ ሁለት ነገሮች ለቀሳውስትና ለዲያቆናት ጥሩ መመሪያዎች ናቸው።

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፣

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፣

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢሮዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፣

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፣

www.ethiopianorthodox.org